## ምዕራፍ 29

# የሞያተኛ እረኞች አሥራ ሁለት ባህሪያት

ሞያተኞች ለገንዘብ የሚሰሩ ሰዎች ናቸው። ለገንዘብ ያላቸው ፍቅር በሚሰሩት ነገር ሁሉ ላይ ተጽዕኖ አለው፡ ፡ የገንዘብ ችግር ባይኖርባቸው እንኳ የሆነ የገንዘብ ጥቅም ከሌለበት ከአንተ ጋር ግንኙነት ማድረግ አይፈልጉም።

ሞያተኞች የትኛውም ሰው ምንም ነገር በነጻ ይሰራል ብለው አያምኑም። ኢየሱስ፣ ሞያተኞች ለበጎች መልካም እንዳይደሉ ጥርት አድርጎ ተናግሯል። እኛም ሞያተኞች እንዳንሆን ሞያተኞች እንዴት እንደሚሰሩ በሚገባ መረዳት ጠቃሚ ነው።

## 1. ሞያተኞች ሁልጊዜ ገንዘብ ይጠይቃሉ።

"ጠግበው የነበሩ ለእንጀራ ሲሉ ተገዙ፤..."

1ኛ ሳሙኤል 2፡5

(ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ 1980)

ሞያተኞች ለገንዘብ ካላቸው ፍቅር የተነሳ ገንዘብ በማያስፈልጋቸው ጊዜ እንኳ ገንዘብ መጠየቃቸውን አያቆሙም። ጠቀም ያለ ክፍያ ካላገኙ ቀላል የተባለ ሥራ እንኳ በነጻ አይሰሩም። ከላይ ያነበብነው ጥቅስ ሞያተኞቹ ጠግበው እንደነበረ ያሳየናል። በሌላ አባባል ምንም ምግብ መመገብ አያስፈልጋቸውም። ያም ሆኖ ግን አሁንም በክፍያ መልክ ዳቦ እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ። አንዳንድ ጊዜ በጣም ሀብታም የሆኑ ሰዎች ሌቦች መሆናቸው አይገርምም? በቂ ነገር አላቸው፣ ነገር ግን ተጨማሪ ነገር ይፈልጋሉ።

## 2. ሞያተኞች ቤተክርስቲያን የሚተክሉት ለገንዘብ ብለው ነው።

"የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለማደስ ድንጋይ ጠራቢዎችንና ዐናጢዎችን...ቀጠሩ።"

2ኛ ዜና መዋዕል 24፡12

ቤተክርስቲያን ይገነባሉ፤ ደግሞም የስብከት፣የማስተማር፣ የጉብኝትና የማማከር አገልግሎት ይሰጡና ለአገልግሎታቸው ክፍያ ይጠይቃሉ። የእግዚአብሔርን ቤት የምትገነባው ከተቀበልከው ደህንነት የተነሳ ልብህ በምስጋና ስለተሞላ መሆን አለበት።የእግዚአብሔርን ቤት የምትገነባው ለእርሱ ካለህ ፍቅር የተነሳ እንጂ በገንዘብ ፍቅር ተነድተህ መሆን የለበትም።

## 3. ሞያተኞች በቤተክርስቲያን ውስጥ ድጋፍ የሚሰጡት ለገንዘብ ብለው ነው።

*"እንዲሁም ቤተ መቅደሱን ለመጠገን የብረትና የናስ ሠራተኞችን ቀጠሩ።"*

2ኛ ዜና መዋዕል 24:12

አሁንም እንደገና ሞያተኞች በቤተክርስቲያን አካባቢ ድጋፍ ሰጪ ሆነው ይታያሉ። ነገር ግን ለሠሩት ሙሉ ክፍያ ይፈልጋሉ። እንዲህ ያሉ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያ እንደመጫወት፣ የቤተክርስቲያንን ህንጻ እንደማስዋብና አንዳንድ እገዛዎችን እንደመስጠት ለመሳሰሉ ሥራዎች የገንዘብ ክፍያን ይቀበላሉ።

## 4. ሞያተኞች በቀላሉ ታማኝነትን ያጎድላሉ

የአሞንም ልጆች አለቆች ጌታቸውን ሐኖንን፦ ዳዊት አባትህን አክብሮ ሊያጽናናህ ባሪያዎቹን ወደ አንተ የላከ ይመስልሃልን? ዳዊትስ ከተማይቱን ለመመርመርና ለመሰለል ለማጥፋትም ባሪያዎቹን የላከ አይደለምን? አሉት።ሐኖንም የዳዊትን ባሪያዎች ወስዶ የጢማቸውን ግሚስ ላጬ፣ ልብሳቸውንም እስከ ወገባቸው ድረስ ከሁለት ቀድዶ ሰደዳቸው።ዳዊትም ያን በሰማ ጊዜ ሰዎቹ እጅግ አፍረው ነበሩና ተቀባዮች ላከ። ንጉሡም። ጢማችሁ እስኪያድግ ድረስ በኢያሪኮ ተቀመጡ፣ ከዚያም በኋላ ተመለሱ አላቸው።የአሞን ልጆች በዳዊት ዘንድ እንደተጠሉ ባዩ ጊዜ፣ የአሞን ልጆች ልከው ከሶርያውያን ከቤትሮዖብና ከሱባ ሀያ ሺህ እግረኞች፣ ከመዓካ ንጉሥም አንድ ሺህ ሰዎች፣ ከጦብም አሥራ ሁለት ሺህ ሰዎች ቀጠሩ።ዳዊትም በሰማ ጊዜ ኢዮአብንና የኃያላኑን ሠራዊት ሁሉ ላከ።የአሞንም ልጆች ወጥተው በበሩ መግቢያ ፊት ለፊት ተሰለፉ የሱባና የረአብ ሶርያውያን፣ የጦብና የመዓካም ሰዎች ለብቻቸው በሰፊ ሜዳ ላይ ነበሩ።ኢዮአብም በፊትና በኋላ ሰልፍ እንደ ከበበው ባየ ጊዜ ከእስራኤል ምርጥ ምርጦቹን ሁሉ መረጠ፣ በሶርያውያንም ፊት ለሰልፍ አኖራቸው። የቀረውንም ሕዝብ በወንድሙ በአቢሳ እጅ አድርጎ በአሞን ልጆች ፊት ለሰልፍ አኖራቸው።ሶርያውያን ቢበረቱብኝ ትረዳኛለህ የአሞን ልጆች ቢበረቱብህ እኔ መጥቼ እረዳሃለሁ።

2ኛ ሳሙኤል 10:3-11

ሞያተኞች ገንዘብ ከመውደዳቸው የተነሳ ርካሽ ሥራዎችንም እንኳ ይሰራሉ። ይህም ማለት ለገንዘብ ሲሉ ለማይረባ ምክንያት ሊክዱህ ይችላሉ ማለት ነው። በምንም ምክንያት ግጭት ይኑር ጥሩ ክፍያ ለሚሰጣቸው ወገነው ይዋጋሉ። የሞያተኛነት መንፈስ ያለበትን ሰው ከቀጠርክ መቼ በስውር ከጠላቶችህ ጋር እንደሚደራደር አታውቅም።

ከላይ ባነበብነው የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ውስጥ ሶሪያውያን ለእነርሱ ምንም ትርጉም በሌለው ጦርነት ውስጥ በአሞን ልጆች እንዴት ተቀጥረው እንደተዋጉ እንመለከታለን። የሄዱት የዳዊት ባሪዎች ጺም በመላጨቱ ምክንያት ወደተቀሰቀሰ ጦርነት ነው። ቅጥረኞች ይህን ይመስላሉ፤ ገንዘብ የሚከፈል ከሆነ ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ አይሉም።

## 5. ሞያተኞች ሁልጊዜ ሁሉም ሰው ስለገንዘብ ብቻ የሚያስብ ይመስላቸዋል።

"እግዚአብሔር ለሶርያውያን የሰረገላና የፈረስየ ብዙም ጭፍራ ድምፅ አሰምቶ ነበር እርስ በርሳቸውም። እነሆ የእስራኤል ንጉሥ የኬጢያውያንና የግብጻውያንን ነገሥት ቀጥሮ አምጥቶብናል ይባባሉ ነበር።"

2ኛ ነገሥት 7:6

እነርሱ ሞያተኞች ስለሆኑ አገልጋይ ሁሉ ለገንዘብ ብሎ እንደሚሰብክ ነው የሚያስቡት። ሌሎችም አገልጋዮች ልክ እንደነርሱ ገንዘብ እንዲወዱ ይጠብቃሉ። ከላይ ያለበበብነው ጥቅስ ሶሪያውያን የእሥራኤል ንጉሥ እነርሱን ለመዋጋት ሰዎችን እንደሚቀጥር ይጠብቁ ነበር። ለገሩ እርሱ ቢፈልግ ገንዘብ ከተከፈላቸው በየትኛውም ምክንያት በተቀሰቀሰ ጦርነት ውስጥ ለመዋጋት የተዘጋጁ ሰዎች እንዳሉ የሚነግረው ሌላ ሰው እስከማያስፈልገው ድረስ ያውቃል።

## 6. ሞያተኞች ለእግዚአብሔር አይጠቅሙም።

"...በዚያም አቤሜሌክ ምናምንቴዎችንና ወሮበሎችን ቀጠረበት፤እነርሱም ተከተሉት።"

መሣፍንት 9:4

መጽሐፍ ቅዱስ ሞያተኞችን ‹‹ከንቱ›› ወይም ‹‹የማይጠቅሙ›› በማለት ይገልጻቸዋል። የአገልግሎቱ ዋና ቀስቃሽ ሞተር ገንዘብ የሆነ ሰው ለእግዚአብሔር አይጠቅምም። ሞያተኛ በመሠረቱ በገንዘብ ተጽዕኖ ሥር ነው። ሞያተኞችን የሚመራቸው እግዚአብሔር ሳይሆን

ገንዘብ ነው! ሞያተኞች ከእግዚአብሔር መመሪያን አይቀበሉም። መመሪያ የሚሰጣቸው ገንዘብ ነው። ለዚህ ነው እንግዲህ ሞያተኛ ለእግዚአብሔር የማይጠቅመው። ሞያተኛ ለገንዘብ ጣዖት እንጂ ለህያው እግዚአብሔር አይጠቅሙም።

## 7. ሞያተኞች ሥር ያልሰደዱ ናቸው።

"...በዚያም አቤሜሌክ ምናምንቴዎችንና ወሮበሎችን ቀጠረበት፤እነርሱም ተከተሉት።"

መሣፍንት 9፡4

ሞያተኞች በመንፈሳዊ ህይወታቸው ሥር የሰደዱ አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ቀላሎች›› በማለት ይገልጻቸዋል። ሥር የሰደደ ሰው ለአገልግሎቱ ከእግዚአብሔር ክፍያ አይጠይቅም። በጥልቀት ብታስቡት ከእግዚአብሔር ያልተቀበልነው ምንም ነገር እንደሌለ መረዳት እንችላለን። ይባሱኑ በእጃችን ያሉ ነገሮች ለጊዜው እንድንጠቀምባቸው የተሰጡን ናቸው። ያለን ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። የተቀበልነውን ነገር ለእግዚአብሔር በክፍያ ለመስጠት ማሰብ ከፍተኛ ሥህተት ነው። እግዚአብሔርን የምትፈራ ከሆነ ምንም አይነት ገንዘብ ከቤተክርስቲያን መቀማት ትፈራለህ።

## 8. ገንዘብ የሞያተኞች ጣዖት ነው።

‹‹...አንጥረኛውን ይቀጥራሉ፤ እርሱም አምላክ አድርጎ ይሠራዋል ለዚያም ይጐነበሱለታል፤ ይሰግዱለትማል።››

ኢሳይያስ 46፡6

ገንዘብ የሞያተኞች ጣዖት ሆኗል። ሞያተኞች ለገንዘብ ብለው ማንኛውንም ነገር ያደርጋሉ። ማገልገል የምትችለው እግዚአብሔርን ወይም ገንዘብን ከሁለት አንዱን ነው! መጽሐፍ ቅዱስ ገንዘብን ከእግዚአብሔር ጋር እንደአማራጭ ማስቀመጡ የሚገርም ነው። እኔ ብሆን አማራጭ አድርጌ የማስቀምጠው ዲያቢሎስን ይሆን ነበር። ኢየሱስ ግን ከእግዚአብሔርና ከገንዘብ አንዱን መምረጥ እንዳለብን ነው የተናገረን!

ዓለም ሁሉ በገንዘብ ቁጥጥር ሥር ነው! ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ ስለሆነ በዓለም ላይ ካለው አብዛኛው ሀብት በሠይጣን ቁጥጥር ሥር ባሉ ክፉ ሰዎች እጅ ነው የሚገኘው።

ለዚህ ነው ሰው ለገንዘብ ብሎ ሲያገለግል ከእግዚአብሔር ጋር የሚለያየው፡፡ ይህ ደግሞ የሞያተኛ ዕድል ፈንታ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ተቆራርጦ ገንዘብን አምላኩ ያደርጋል፡፡

## 9. ሞያተኞች የሀብታሞች ቅጥረኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

"እርሱም፡-ሚካ እንዲህ እንዲህ አደረገልኝ፥ ቀጠረኝም፥ እኔም ካህን ሆንሁለት አላቸው፡፡"

መሣፍንት 18፡4

ሞያተኛ መጋቢዎች ብዙ ጊዜ ለሀብታሞች ‹የግል ነብይ› ሲሆኑ ይታያሉ፡፡ ሞያተኛ መጋቢዎች ለሀብታም አለቆቻቸው ይዘምራሉ ምስጋናም ያቀርባሉ መልካም ብቻ የሚያወሳ ትንቢትም ይናገሩላቸዋል፡፡ ጥሩ መጋቢ ለመሆን ገንዘብ ከሚሰጡህ ሀብታሞች ተጽዕኖ ነጻ መሆን አለብህ፡፡

## 10. ሞያተኞች ለትንሽ ነገር ብለው እግዚአብሔርን ላይታዘዙ ይችላሉ፡፡

"የእስራኤልን ልጆች በእንጀራና በውኃ ስላልተቀበሉአቸውና ይረግማቸው ዘንድ በለዓምን ስለ ገዙባቸው ነው ነገር ግን አምላካችን እርግማኑን ወደ በረከት መለሰው።"

ነህምያ 13፡2

ሞያተኞች ለገንዘብ ብለው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ሲሄዱ ይችላሉ፡፡ ሞያተኛ ለገንዘብ ብሎ ከእግዚአብሔር ጋር ሊዋጋ እንኳ ይችላል፡፡ በለዓም እግዚአብሔር የባረከውን ህዝብ ሊረግም ሞክሮ ነበር፡፡

## 11. ሞያተኞች በገንዘብ እንጂ በእግዚአብሔር አይመሩም፡፡

"እግዚአብሔርም ልኮት እንዳልነበረ፥ በእኔ ላይ ግን ትንቢት እንደ ተናገረ፥ እነሆ፥ አወቅሁ ጦብያና ሰንባላጥም ገዝተውት ነበር። ይህንም ነገር አደርግና እበድል ዘንድ፥ በእኔም ላይ ክፉት እንዲናገሩና እንዲያላግጡ ያስፈራራኝ ዘንድ ተገዝቶ"

ነህምያ 6፡12-13

ሞያተኞች በእግዚአብሔር ያልተጠሩና ያልተላኩ ናቸው፡፡ ገንዘብ ነው ‹‹የጠራቸው››፡፡ ‹‹የተላኩትም›› በገንዘብ ነው፡፡ ሞያተኛ አገልጋይ የሚከተለው የአገልግሎት አቅጣጫ የሚወሰነው በሚያስገኘው የገንዘብ መጠን ላይ ነው፡፡

ብዙ ነፍሳትን ለክርስቶስ የሚማርኩበት አቅጣጫ እንኳ ቢሆን ገንዘብ የማያስገኝ ከሆነ አይሄዱም። እውነተኛ አገልግሎት ሊሰጡ ወደማይችሉበት ነገር ግን ገንዘብ ወደሚያስገኝ ሥፍራ ይሄዳሉ። ሞያተኞች የሚፈልጉት ነገር ቢኖር ገንዘብ ብቻ ነው።

ሰዎች ለገንዘብ ብለው ቤተክርስቲያን ሲጀምሩ ተመልክቻለሁ። ከሚሰበሰበው መባ መካፈል ይፈልጉ ነበር። ገንዘብን እንጂ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አይፈልጉም። ሞያተኞች የሚያደርጉትን ነገር መንፈሳዊ የሚመስል ምክንያት ማላበስ ይወዳሉ። ለንባላጥና ጥብያ ትንቢት የሚናገርላቸው ሰው ቀጥረው ነበር። እነኚህ ሰዎች እግዚአብሔር እንደተናገራቸው አድርገው ያወሩ ነበር። መንፈስ ቅዱስ እንደሚመራቸው ይናገራሉ እንጂ አብረው የገነቡትን ቤተክርስቲያን እንዲያፈርሱ የሚመራቸው ገንዘብ ነው።

## 12. ሞያተኞች የእግዚአብሔርን ሥራ ያሰናክላሉ

> **ከፋርስ ንጉሥ ከቂሮስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከ ፋርስ ንጉሥ እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ድረስ ዕቅዶቻቸውን የሚያሰናክሉ መካሪዎችን በገንዘብ ገዙባቸው።**
>
> **ዕዝራ 4፡5 (ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመው 1980)**

ሞያተኞች በእውነት ‹‹ጥሪ ያላቸው›› ስላልሆኑና የእውነተኛው አገልግሎት አካል ስላይደሉ በመሠረቱ እውነተኛውን አገልግሎት የሚያሰናክሉ ናቸው።ለገንዘብ ብለን ስንሰብክ ‹‹ዓለም›› እንኳ ሳይቀር በውስጣችን ያለውን ስግብግብነት ይመለከታል።

ግያዝ እውነተኛን አገልግሎት ስለሚያሰናክል ሰው ጥሩ ምሳሌ ነው። ግያዝ ለገንዘብ ብሎ በማገልገሉ ንዕማን ኤልሳዕ ለገንዘብ የሚስገበገብ እንደሆነ እንዲያስብ አድርጎታል። ይህን በማድረጉም የእግዚአብሔርን ሥራ አጎደፈ። ‹‹መጋቢዎች ለገንዘብ ይሮጣሉ›› የሚለውን የተለመደ አባባል እውነት ነው እንዲባል ምክንያት የሚሆኑ መጋዎች አሉ። አህዛብ የሆነው ንዕማን የግያዝን ስግብግብነት ተገንዝቦ ከጠየቀው የበለጠ እንዲወስድ ለመነው። "እርሱም፦ ደኅናነው። አሁን ከነቢያት ወገን የሆኑት ሁለት ጕልማሶች ከተራራማው ከኤፍሬም አገር ወደ እኔ መጥተዋል አንድ መክሊት ብርና ሁለት መለወጫ ልብስ ትሰጣቸው ዘንድ እለምንሃለሁ ብሎ ጌታዬ ላከኝ አለ። ንዕማንም ሁለት መክሊት ትወስድ ዘንድ ይፈቀድልህ አለ ግድ አለውም ሁለቱንም መክሊት ብር በሁለት ከረጢት ውስጥ አሰረና ከሁለት

መለወጫ ልብስ ጋር ለሁለት ሎሌዎቹ አስያዘ እነርሱም ተሸክመው በፊቱ ሄዱ።" (2ኛ ነገሥት 5:22-23)

## ምዕራፍ 30

# ዘጠኝ የሞያተኛ መጋቢ አይነቶች

ሞያተኛ ማለት የእግዚአብሔርን ሥራ ሲሠራ ክፍያን የሚጠይቅ ማለት ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ ፍሬ እንዲያፈሩና ለእግዚአብሔር እንዲሠሩ ተጠርተዋል። በዚህም ምክንያት የትኛውም የክርስቲያኖችና የአገልጋዮች ክፍል ለሞያተኛነት ሊጋለጥ ይችላል።

ህይወታችን ጤናችን፣ ገንዘባችንና ባጠቃለይ በዚህ ምድር መኖራችን በእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ነው። ሁሉንም ከእርሱ የተቀበልን ስለሆነ በቤቱ ለምንሰጠው አገልግሎት ክፍያ ልንጠይቀው አይገባም። በየትኛውም መልኩ ለእርሱ መሥራት ታላቅ መታደል ነው። የተጠራንበት እያንዳንዱ አይነት አገልግሎቶች (ቴክኒካል፣ መንፈሣዊ፣ የገንዘብ፣ህጋዊ፣ የሙዚቃ) ክብር ነው።

ሽልማት የምንፈልግ ከሆነ በሰማይ እንጂ በምድር ልንጠባበቅ አይገባም! ሰማይ ፍርድ የሚሰጥበት፣እረፍት ያለበትና ሽልማት የምንቀበልበት ሥፍራ ነው። ምድር ግን የሥራ፣የሥራ፣ የሥራ ቦታ ነው። ዋጋህን በምድር ለመቀበል የግድ የምትል ከሆነ የሰማይ ሽልማትህን የማግኘት መብትህን ልታጣ ትችላለህ።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ባለኝ ቆይታ ከብዙ የተለያዩ አይነት ሞያተኞች ጋር የመገናኘት ዕድል ገጥሞኛል።

ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ቤት ክፍያን የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ከእነኚህ የተለያዩ አይነት ሞያተኞች መካከል የተወሰኑትን መዝግቦ መያዙ በጣም ያስገርማል።

### 1. ባለጠጋ ሞያተኞች

"ጠግበው የነበሩ እንጀራ አጡ ተርበው የነበሩ ከራብ ዐርፈዋል መካኒቱ ሰባት ወልዳለችና፣ ብዙም የወለደችው ደከማለች።ጠግበው የነበሩ ለእንጀራ ሲሉ ተገዙ፤"

1ኛ ሳሙኤል 2፡5 (የ1980 አዲስ ትርጉም)

እነኚህ ሰዎች የገንዘብ ችግር የሌለባቸው ሆነው ሳለ ለሚሰሩት ለእያንዳንዱ ነገር ክፍያ የሚጠይቁ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ጠግበዋል፣ነገር ግን አሁንም የማያስፈልጋቸውን ዳቦ ለማግኘት ለገንዘብ ይቀጠራሉ።

ለምሣሌ ያህል የቤተክርስቲያን ገንዘብ የማያስፈልገው ሀብታም አርክቴክት ወይም መሐንዲስ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን ሙያውን የተመለከተ ሥራ ለቤተክርስቲያን ከሰራ ክፍያ ይጠይቃል።

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም የቤተክርስቲያን ገንዘብ የማያስፈልግው ሀብታም ጠበቃ አንድ አነስተኛ የኮንትራት ውል ካዘጋጀ ክፍያ ይጠይቃል። በእርግጥ እነኚህ ሰዎች ሀብታሞች ሆነው ሳለ የሚያገለግሉት ጌታን መሆኑን ካለመረዳት የተነሳ ለሠሩት ሥራ ሁሉ ክፍያን ይጠይቃሉ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ከቤተክርስቲያን ደሞዝ መውሰድ የማያስፈልጋቸው ነገር ግን ማንኛውም ነገር በነፃ በመሥራት ስለማያምኑ ከቤተክርስቲያን ገንዘብ ድርሻቸውን መውሰድ የሚፈልጉም አሉ።

## 2. ባለሙያ ሞያተኞች

"እነርሱም የእግዚአብሔርን ቤት ለማደስ ድንጋይ ጠራቢዎችንና አናጢዎችን ...ቀጠሩ።"

2ኛ ዜና መዋዕል 24፥12 (የ1980 አዲስ ትርጉም)

ባለሞያ ሞያተኞች ማለት የተለየ ክህሎትና ችሎታ ያላቸው ሰዎች ማለት ነው። ለዚህ ምሣሌ የሚሆነው በየእሁድ አምልኮ ጊዜ ፒያኖ ስለሚጫወት ክፍያ የሚጠይቅ የሙዚቃ ባለሙያ ነው። የድምጽ መቆጣጠሪያውን በመጠቀም የድምጽ መጠን ስለጨመሩና ስለቀነሱ ክፍያ የጠየቁ አገልጋዮች አጋጥመውኛል። ለመዘመር ልምምድ ለመምጣት ክፍያ የሚጠይቁ መዘምራንም አሉ።

በቤተክርስቲያን ህንጻ ውስጥ በሚገኝ መጸዳጃ ቤት ውስጥ የላላ ብሎን ቢያዩ ክፍያ ካላገኙ ለማጥበቅ ፈቃደኛ ያልሆኑ የቧንቧ ሠራተኞችና የኤሌክትሪክ ባሙያዎች አሉ። ጠበቆች፣ ሐኪሞች፣ ኢንጂነሮች፣አርክቴክቶች እና ሌሎችም የተለያዩ ሙያዎች ያላቸው ሰዎች በዚህ ምድብ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ አንተ ሰው ያልተቀበልከው ምን አለ?›› እንደሚል ያለን ነገርና እውቀታችን ሁሉ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ስጦታ ነው። እርሱን

በማገልገል ምሥጋናችንን ለመግለጽ የምንችልበት የትኛውንም ዕድል ካገኘን በሙሉ ልባችን እናድርገው፡፡

## 3. ቅጥር ወታደር ሞያተኛ

"ከዚህ በኋላ የአሞን ልጆች ንጉሥ ሞተ፥ ልጁም ሐኖን በፋንታው ነገሠ። ዳዊትም፦ አባቱ ወረታ እንዳደረገልኝ እኔ ለናዖስ ልጅ ለሐኖን ቸርነት አደርጋለሁ አለ። ዳዊትም አባቱ ስለ ሞተ ሊያጽናናው ባሪያዎቹን ላከ የዳዊትም ባሪያዎች ወደ አሞን ልጆች አገር መጡ። የአሞንም ልጆች አለቆች ጌታቸውን ሐኖንን፦ ዳዊት አባትህን አክብሮ ሊያጽናናህ ባሪያዎቹን ወደ አንተ የላከ ይመስልሃልን? ዳዊትስ ከተማይቱን ለመመርመርና ለመሰለል ለማጥፋትም ባሪያዎቹን የላከ አይደለምን? አሉት። ሐኖንም የዳዊትን ባሪያዎች ወስዶ የጢማቸውን ገሚስ ላጨ፥ ልብሳቸውንም እስከ ወገባቸው ድረስ ከሁለት ቀድዶ ሰደዳቸው። ዳዊትም ያን በሰማ ጊዜ ሰዎቹ እጅግ አፍረው ነበሩና ተቀባዮች ላከ። ንጉሡም። ጢማችሁ እስኪያድግ ድረስ በኢያሪኮ ተቀመጡ፥ ከዚያም በኋላ ተመለሱ አላቸው። የአሞን ልጆች በዳዊት ዘንድ እንደተጠሉ ባዩ ጊዜ፥ የአሞን ልጆች ልከው ከሶርያውያን ከቤትሮዖብና ከሱባ ሀያ ሺህ እግረኞች፥ ከመዓካ ንጉሥም አንድ ሺህ ሰዎች፥ ከጦብም አሥራ ሁለት ሺህ ሰዎች ቀጠሩ።"

2ኛ ሳሙኤል 10፡1-6

ቅጥር ወታደር በክፍያ የሚዋጋ ወታደር ነው፡፡ ለክብር ወይም ለታላቅ ብሔራዊ ዓላማ አይዋጋም፡፡ ለገንዘብ ሲል ብቻ የሚዋጋ ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ላሉ ቅጥር ወታደሮች ምሳሌ የሚሆኑን የጸሎት ጓድና በመንፈስ የማይጋደሉ ሰዎች ናቸው፡፡ የዚህ አይነቶቹ ሰዎች የሚጸልዩት በርካታ ገንዘብ እስከተከፈላቸው ድረስ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ደሞዝ ስለሚከፈላቸው ብቻ የወንጌል ሥርጭት ሥራ የሚሰሩ ሰዎችም አሉ፡፡ ነቢያት፣ መጋቢዎች፣ አስተማሪዎች መልካሙን ገድል ለገንዘብ ብለው የመጋደል ፈተና ውስጥ ሲገቡ ከሚችሉት መካከል ይገኙበታል፡፡

"እግዚአብሔር ለሶርያውያን የሰረገላና የፈረስ የብዙም ጭፍራ ድምፅ አሰምቶ ነበር እርስ በርሳቸውም። እነሆ፥ የእስራኤል ንጉሥ የኬጢያውያንና የግብጻውያንን ነገሥት ቀጥሮ አምጥቶብናል ይባባሉ ነበር።"

2ኛ ነገሥት 7፡6

## 4. ምናምንቴና ወሮበላ ሞያተኞች

"ከበአልብሪትም ቤት ሰባ ብር ሰጡት በዚያም አቤሜሌክ ምናምንቴዎችንና ወሮበሎችን ቀጠረበት፥ እነርሱም ተከተሉት።"

መሣፍንት 9፡4

ምናምንቴዎችና ወሮበሎች በቤተክርስቲን ውስጥ የሚገኙ በርካታ ቁጥር ያላቸው መንፈሳዊ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው። የአንድን ነገር ዘላለማዊ ገጽታ የሚረዱት ከስንት አንዴ ነው። እንኚህን ሰዎች በምታስተውልበት ጊዜ ሀሳባቸው ሁልጊዜ በአንድ አቅጣጫ ብቻ የተቃኘ ነው።

ለእነኚህ ሰዎች ቤተክርስቲያን የንግድ ጥሩ አጋጣሚ ነች። የቻሉትን ያህል ከቤተክርስቲያን ለማግኘት ይጥራሉ። የምናምንቴነትና የወሮበላነት መንፈስ ያለባቸው ሞያተኛ አገልጋዮች ከቤተክርስቲያን የቻሉትን ያህል ገንዘብ ለመበዝበዝ ይበረታታሉ።

## 5. አማካሪ ሞያተኞች

"ከፋርስ ንጉሥ ከቂሮስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከ ፋርስ ንጉሥ እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ድረስ ዕቅዶቻቸውን የሚያሰናክሉ መካሪዎችን በገንዘብ ገዙባቸው።"

ዕዝራ 4፥5 (ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመው 1980)

እነኚህ ደግሞ የማማከር አገልግሎት በጌታ ቤት ውስጥ የሚሰጡ ናቸው። ምናልባት የጋብቻ አማካሪዎች ወይም የቃሉ አስተማሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ከሚያደርጉትና ከሚሰጡት የምክር አገልግሎት ሁሉ ጋር የክፍያ ጥያቄ ያቀርባሉ።

ኢየሱስ ስለሞያተኞች ጥሩ ነገር ስላልተናገረ የተለያዩ አይነት ሞያተኞችን ለይተን ማወቃችን ይጠቅመናል። ኢየሱስ ሞያተኞች ለሚያገለግሏቸው ሰዎች ግድ የማይላቸው እንደሆኑ አስተምሮናል። ስለአንተ ምንም ግድ በማይሰጠው ሀኪም የህክምና ክትትል እንዲደረግልህ ትወዳለህን? አገልጋዮች ግድ የማይሰጣቸው ሲሆኑ የአገልግሎት እውነተኛ መልክ ይቀየራል።

## 6. ሐሰተኛ ነቢያት ሞያተኞች

"እግዚአብሔርም ልኮት እንዳልነበረ፥ በእኔ ላይ ግን ትንቢት እንደ ተናገረ፥ እነሆ፥ አወቅሁ ጦብያና ሰንባላጥም ገዝተውት ነበር።"

ነህምያ 6፥12

በአንድ ወቅት (በነብይ) የምትመራ ቤተክርስቲያን ጎበኘሁ። በጉብኝቴም የትንቢት አገልግሎት በቤተክርስቲያን አባላት ላይ የሚያመጣውን ለውጥ ለመረዳት ቻልኩ።

አብዛኛዎቹ የቤተክርስቲያኒቱ አባላት በዚህ ቀጥተኛ የሆነ የመገለጥ ቃል በሚናገር ነቢይ ተመስጠው ነበር፡፡

አስገራሚ የሆነው ስጦታው ከእርሱ በሐብት የሚበልጡ እና ከእርሱ ይልቅ በትምሕርት የገፉ ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያኒቱ ስቧል፡፡ ወደዚህ ወዳልተማረ ነቢይ አገልግሎት በተሳቡት ሰዎች ደረጃ በጣም እገረም ነበር፡፡ የትንቢት ስጦታው ያሉበትን ጉድለቶች እንደሸፈነ አስተዋልኩ፡፡

መቼ ልጅ እንደሚያገኝ በትክክል ስለነገረው በዚህ መጋቢ አገልግሎት ህይወቱ ፈጽሞ እንደተለወጠ አንዱ አጫወተኝ፡፡

እንዲህ ያለው እውነተኛ ነቢይ ወደ ሀሰተኛ ነቢይት ሊቀየር የሚችልባቸው ሁኔታዎች እንደሚኖሩ መረዳት አያዳግትም፡፡ የሚያመጣው መገለጥ ትክክለኛነት በጨመረ ቁጥር የበለጠ ተጠቃሚና ሀብታም እየሆነ መምጣቱ አይቀርም፡፡

በዚህም ምክንያት ሰዎችን ለማስደነቅ የተለዩ ትንቢቶችንና መገለጦችን ለማምጣት መፈተን ሊከሰት ይችላል፡፡ እውነተኛ ነቢያት የሚስቱት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ሀሰተኛ ነቢይ ለአገልግሎት የሚቀሰቀሰው በገንዘብ ፍላጎት ነው፡፡ በዋነኛነት ለአገልግሎት የሚያነሳሳህ ገንዘብ ከሆነ ለገንዘብ ብለህ እንጂ እግዚአብሔርን ወክለህ ልትናገር አትችልም፡፡

## 7. ዝነኛ ሞያተኞች

> "ከግብፅ በወጣችሁ ጊዜ እንጀራና ውኃ ይዘውበመንገድ ላይ አልተቀበሉአችሁምና፥ በመስጴጦምያ ካለው ከፋቱራ የቢዖርን ልጅ በለዓምን ዋጋ ሰጥተው ይረግምህ ዘንድ አምጥተውብሃልና፡፡"
>
> ዘዳግም 23፡4

> "የእስራኤልን ልጆች በእንጀራና በውኃ ስላልተቀበሉአቸውና ይረግማቸው ዘንድ በለዓምን ስለገዙባቸው ነው ነገር ግን አምላካችን እርግማኑን ወደ በረከት መለሰው፡፡"
>
> ነህምያ 13፡2

አንዳንድ ሞያተኞች ዕውቅና የሚያገኙት ተጨባጭ የሆነ ኮንትራት ሲፈራረሙ፡፡ ነቢዩ በለዓም ያን ያህል የታወቀ ሙያተኛ አልነበረም፡፡ እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ ጊዜ ነው ታዋቂ የሆነው፡፡

እንግዳ በሆነ ሁኔታ አህያ በመንገዱ ላይ መቆሟም እንዲታወቅ አድጎታል:: በተጨማሪም እግዚአብሔር የባረካቸውን ማንም ሊረግማቸው እንደማይችል ማሳያ መሆኑም እንዲታወቅ አድርጎታል:: በለዓም ለጥቂት ገንዘብ ብለው የሚተነብዩ ነቢያት ሀሰተኞች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ምሳሌ ነው::

## 8. መጋቢ ሞያተኞች

"እርሱም፦ ሚካ እንዲህ እንዲህ አደረገልኝ፥ ቀጠረኝም፥ እኔም ካህን ሆንሁለት አላቸው።"

መሣፍንት 18:4

አገልግሎታቸውን በገንዘብ ብቻ የሚሰጡ መጋቢዎችም አሉ:: እንዲህ ያሉ መጋቢዎች ለሀብታሞች ለየት ያለ የማማከር አገልግሎት ይሰጣሉ:: ሞያተኛ መጋቢዎች ለሀብታሞች የግል የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራም ማዘጋጀት እንደሚወዱ ትመለከታለህ::

የኢየሱስ አገልግሎት በአብዛኛው ለድሆች ነው፤ ስለሆነም የተለየ አገልግሎት እንዲዘጋጅላቸው ለማድረግ አቅም ለሌላቸው ሁሉ መዳረስ አለበት:: እነኚህ ቅጥረኛ መጋቢዎች ለሀብታሞቹ አባሎቻቸው እውነቱን ሁሉ ይነግሯቸው እንደሆን አላውቅም! እናንተንና ቤተሰባችሁን የሚመግብን ሰው ክፉም ቢሆን መርገም ይከብዳል::

## 9. ረዳት መጋቢ ሞያተኞች

እርሱም፦ ደኅና ነው። አሁን ከነቢያት ወገን የሆኑት ሁለት ጕልማሶች ከተራራማው ከኤፍሬም አገር ወደ እኔ መጥተዋል አንድ መክሊት ብርና ሁለት መለወጫ ልብስ ትሰጣቸው ዘንድ እለምንሃለሁ ብሎ ጌታዬ ላከኝ አለ።

ንዕማንም። ሁለት መክሊት ትወስድ ዘንድ ይፈቀድልህ አለ ግድ አለውም ሁለቱንም መክሊት ብር በሁለት ከረጢት ውስጥ አስረና ከሁለት መለወጫ ልብስ ጋር ለሁለት ሎሌዎቹ አስያዘ እነርሱም ተሸክመው በፊቱ ሄዱ።

2ኛ ነገሥት 5:22-23

ገንዘብን የሚጎመጅ ረዳት መጋቢ ግያዝ ትክክለኛ ምሳሌ ነው:: የኤልሳዕ ረዳት በመሆኑ የኤልሳዕን ቅባት የመውረስ ዕድል ነበረው::

ለሰጠው አገልግሎት ገንዘብ የማግኘት ምኞቱ የወደፊት አገልግሎቱን አበላሸበት።

ረዳት መጋቢዎችም ለገንዘብ ራሳቸውን ሊሸጡ ይችላሉ። በአንድ ወቅት ከፍተኛ የደሞዝ አማራጭ የቀረበለትን አንድ ረዳት መጋቢ አስታውሳለሁ። ይህ መጋቢ የቀረበለትን የደሞዝ አማራጭ ሲያገኘው ከነበረው የተሻለ ስለሆነ ብቻ ያለማመንታት ተቀበለ። ወደኋላ ላይ ግን የቀጠረው ሰው ክፉ እንደሆነ ተረዳ። መጋቢዎች ከፍተኛ ደሞዝ አሳዳጆች ናቸው ወይስ እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚጥሩ ናቸው?

*ምዕራፍ 31*

# ቅር የሚያሰኙ እረኞች

በአገልግሎት ውስጥ ብዙ ቅር የሚያሰኙ ነገሮች አሉ። ብዙ የወንጌል አገልጋዮች በታላቅ ጉጉት ወደ አገልግሎት ይገባሉ። በታላቅ ደስታና ናፍቆት ይሾማሉ። ነገር ግን ከጊዜ በኋላ ዋና ቅር የሚያሰኙ ይሆናሉ። ንጉሥ ሳዖል ‹‹ቅር ስለሚያሰኙ እረኞች›› ጥሩ ማሳያ ነው። ነቢዩ ሳሙኤልንና እግዚአብሔርን ተስፋ ያስቆረጠ ነበር። እግዚአብሔር እርሱን በማንገሱ ተጸጸተ። አንተስ አንድ ቀን እግዚአብሔር ቅር ይሰኝብህ ይሆን?

## አሥራ ሦስት የተስፋ አስቆራጭ እረኞች ምልክቶች

የእግዚአብሔርም ቃል። ሳኦል እኔ ከመከተል ተመልሶአልና፥ ትእዛዜንም አልፈጸመምና ስላነገሥሁት ተጸጸትሁ ብሎ ወደ ሳሙኤል መጣ። ሳሙኤልም ተቈጣ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። ሳሙኤልም በነጋው ሳኦልን ለመገናኘት ማለደ። ሳኦልም ወደ ቀርሜሎስ መጣ እነሆም፥ የመታሰቢያ ዓምድ ባቆመ ጊዜ ዞሮ አለፈ፥ ወደ ጌልገላም ወረደ የሚል ወሬ ለሳሙኤል ደረሰለት። ሳሙኤልም። ይህ በጆሮዬ የምሰማው የበጎች ጩኸትና የበሬዎች ግሣት ምንድር ነው? አለ።

1ኛ ሣሙኤል 15፡11-14

## 1. ቅር የሚያሰኙ መጋቢዎች ከሾምካቸው በኋላ እንድትጸጸት ያደርጉሀል።

"ሳኦል እኔ ከመከተል ተመልሶአልና፥ ትእዛዜንም አልፈጸመምና ስላነገሥሁት ተጸጸትሁ።"

1ኛ ሣሙኤል 15፡11

ቅር የሚያሰኝ መጋቢ ዋነኛ ምልክት እርሱን በመሾምህ መጸጸትህ ነው። መጋቢ ስላደረከው ትጸጸታለህ! እርሱን የወንጌል አገልጋይ ነው ብለህ ለሌላ ሰው በማስተዋወቅህ ትጸጸታለህ። መጋቢ ብዬ ባልሾምኳቸው ምን ነበረበት? ብዬ የማስባቸውን አንዳንድ ሰዎችን በትክክል አስታውሳለሁ። አንድ ልብ ልትለው የሚገባ ነገር አለ፤ ሰዎች ሆን ብለው ቅር የሚያሰኙ የመሆን ፍላጎት የላቸውም ወይም

በአንድ ጀንበር እንደዚያ አይሆኑም። ወደኋላ ላይ እንደምንመለከተው ቅር የሚያሰኙ የሚሆኑባቸው ምክንያቶች አሉ።

## 2. ቅር የሚያሰኙ እረኞች መሪያቸውን የሚከተሉት የተወሰነ ርቀት ብቻ ነው፡ ሙሉ በሙሉ አይከተሉትም።

"ሳኦል እኔን ከመከተል ተመልሶአልና፥ ትእዛዜንም አልፈጸመምና ስላነገሥሁት ተጸጸትሁ።"

1ኛ ሳሙኤል 15፡11

ከሚሰጣቸው መመሪያ ከፊሉን ይተገብሩና የተቀረውን ይተዉታል። በከፊል መከተል ወደሚፈለገው ደረጃ አያደርስም። ሰዎች ሙሉ በሙሉ ሳይከተሉት ይቀሩና አንዳንድ ችግር ሲገጥማቸው እርሱን መከተል ስህተት እንደሆነ ያስባሉ። ብዙ ጊዜ ሰዎች ለአገልግሎት ሲጠሩ ወይም ሲመደቡ የስኬት ጫፍ የደረሱ ይመስላቸዋል። ነገር ግን በዚህ ምድር ያለ ማንም ገና የስኬት ጫፍ አልደረሰም፤ ማንም የበቃ እውቀት የለውም።

መንግስተ ሰማያት እስከምንደርስ ድረስ ማንም በቂ ፍሬ አፍርቷል ብሎ መናገር አይቻልም። ወደዚያ እስከምንደርስ ድረስ ሁላችንም ተማሪዎች ነን። የትም እንደደረስን ማሰብ የለንም። በቅርቡ ምንም አያስፈልገኝም ብሎ ማሰብ ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ጌታ ተናገረኝ፡ ፡ ‹‹ ምንም አያስፈልገኝም የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ልብ ውስጥ የነበረ ሀሳብ ነው። ተነሳና አንድ ነገር አድርግ! ተነሳና አንድ ነገር ግዛ›› አለኝ። ምንም አያስፈልገኝም ብለህ ለራስህ አትንገር።

## 3. ቅር የሚያሰኙ እረኞች ለመጋቢዎቻቸው መመሪያና ትዕዛዝ አይገዙም።

"ሳኦል እኔ ከመከተል ተመልሶአልና፥ ትእዛዜንም አልፈጸመምና ስላነገሥሁት ተጸጸትሁ።"

1ኛ ሳሙኤል 15፡11

የራሳቸውን ሀሳብ የተከተሉና ወደየትም መድረስ ያልቻሉ ሰዎችን ተመልክቻለሁ። ለሚሲዮናዊነት ሥራ የላኳቸውንና በኋላም የገመገምኳቸውን የሚሲዮናዊያን ቡድን አስታውሳለሁ። እናንተ ምናልባት ምክር ልትሏቸው የምትችሉት አንዳንድ መመሪያዎችን ሰጥቻቸው ነበር። ከእነዚያ ሚሲዮናዉያን መካከል ሁለቱ

መመሪያውን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ በማድረጋቸው ታላላቅ፣ የሚያድግና ውጤታማ ቤተክርስቲያናትን መመስረት ችለው ነበር።

ቀሪዎቹ ሚሲዮናውያን ግን ጥቂት ሰዎችን ይዘውና ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ገጥሟቸው ሲንገታገቱ ነበር። በእነዚህ ሚሲዮናዊያን መካከል የነበረው ልዩነት ምንድነው? ሁለቱ ሚሲዮናዊያን ምክሬን አንድም ቃል ሳይቀር መከተል እንዳለባቸው የተቀበሉ ሲሆን ሌሎቹ ግን ምክሮቼን ለመከተል ብዙም ጥረት አላደረጉም ነበር። አንዳንድ ጊዜ መመሪያዎች መንፈሳዊ ላይመስሉ ይችላሉ። ነገር ግን ትርፋማ የሚያደርጉህ እነሱ ናቸው። ካንተ ይልቅ ልምድ ያላቸውን አባቶች መመሪያና ምክር አንድም ሳይቀር በጥንቃቄ ተግባራዊ አድርግ።

ሳዖል በግልጽ ስህተት ሰርቶ ሳለ ምንም ስህተት እንዳልፈጸመ ከሳሙኤል ጋር መከራከሩን ቀጠለ።

> **"ሳኦልም፡- ሕዝቡ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ይሠዉአቸው ዘንድ መልካሞቹን በጎችና በሬዎች አድነዋቸዋልና ከአማሌቃውያን አምጥተዋቸዋል፤ የቀሩትንም ፈጽመን አጠፋን አለው።"**
>
> **1ኛ ሳሙኤል 15:15**

ቅር የሚያሰኙ (ሳዖል መሰል) መጋቢዎች ስህተት መስራታቸውን ፈጽሞ አይቀበሉም። ራሳቸውን የሚያታልሉና ስህተታቸውን የማያምኑ ናቸው። ፍጥጥ ያለ ማስረጃ እያለ እንኳን፣ ሳዖል መሠል መጋቢዎች ንስሐ አይገቡም። ስህተት በሰራህ ጊዜ ‹‹ይቅርታ›› መጠየቅ እጅግ አስፈላጊ ነው። ወደ አገልግሎት የተጠራኸው ፍጹም ስለሆንክ አይደለም። ወደ አገልግሎት የተጠራኸው ፈጽሞ ስህተት ስለማትሰራ አይደለም።

በስህተት የተሞላን ብንሆንም እግዚአብሔር አሁንም ይጠቀምብናል። ፍጹም የሆነ ማንነት ለማግኘት መታገል አስፈላጊ አይደለም። አንተም እኔም ፍጹማን አይደለንም። ሳዖል ራሱን መከላከሉን ቀጥሎ የሳሙኤልን የምርመራ ውጤት ለመቀበል እምቢ አለ። ያ ነው ወደ ጥፋት የመራው።

## 4. ቅር የሚያሰኙ እረኞች የሚከፍሉትን መስዋዕት የሚመርጡት ራሳቸው ናቸው።

እነኚህ እረኞች መጋቢያቸውን ከመታዘዝ ይልቅ መስዋዕትነትን የሚጠይቁ የሚመስሉ ሌሎች ነገሮችን ሲያደርጉ ይገኛሉ። ስለሆነም ተቀባይነት የሌለው፣የማይፈለግ ወይም ፈጽሞ የማያስፈልግ መስዋዕትን ያቀርባሉ። ብዙ ጊዜ አንድ ወይም ሁለት የሚጠበቁ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ይኖራሉ። ሁልጊዜ አለቃህን በሚያስደስቱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አለማድረግ ስህተት ነው።

## 5. ቅር የሚያሰኙ መጋቢዎች ለአገልግሎት ከተሾሙ በኋላ ራሳቸውን እንደ በግ አይቆጥሩም።

መጋቢዎችም ሊመሩና አቅጣጫ የሚያሳያቸው ያስፈልጋቸዋል። ምንግዜም ቢሆን ራስህን እንደ አነስተኛ ግልገል መቁጠር አለብህ። ቅር የሚያሰኙ መጋቢዎች ወደ አገልግሎት ከመጡ በኋላ ራሳቸውን እንደበግ መቁጠራቸውን ያቆማሉ። ራስህን የማያቋርጥ ምሪት እንደሚያስፈልገው ትንሽ በግ አድርገህ ማየት በጣም ጠቃሚ ነው። የተሾምክ ቢሆንም የሚመራህና አቅጣጫ የሚያሳይህ ያስፈልግሀል። ሁልጊዜ አቅጣጫ የሚያሳየኝ እንደሚያስፈልገኝ ጠንቅቄ አውቃለሁ። ምንም እንኳ በእኔ ስር ብዙ ቤተክርስቲያኖች ቢኖርም እጅግ የሚያስፈልገኝ እንደሆነ ስለማምን ምሪትን ለመቀበል እጸልያለሁ።

## 6. ቅር የሚያሰኙ መጋቢዎች በአይኖቻቸው ፊት ታናሽ መሆን ያቆማሉ።

> "ሳሙኤልም ሳኦልን፦ ቆይ፥ እግዚአብሔር ዛሬ ሌሊት የነገረኝን ልንገርህ አለው እርሱም፦ ተናገር አለው።
>
> ሳሙኤልም አለ። በዓይንህ ምንም ታናሽ ብትሆን ለእስራኤል ነገዶች አለቃ አልሆንህምን? እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ንጉሥ ትሆን ዘንድ ቀባህ።"
>
> 1ኛ ሳሙኤል 15፡ 16-17

‹‹እናቴ ´በዓይንህ ፊት ሁልጊዜ ታናሽ እንደሆንክ ብታስብ መልካም ይሆንልሀል' አለችኝ›› በማለት አንድ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው በአንድ ወቅት የተናገሩትን ምንግዜም አይረሳኝም። እናቱ የሰጠችው ምክር ለአንድ መጋቢ ሊሰጥ ከሚችል ምክር በብዙ የላቀ ነው። ምንግዜም ታናሽነትህን አትዘንጋ፣ለመማር የተዘጋጀህ ሁን፣ እንዲሁም ሁል ጊዜ ባዶ ሁን! በሌላ አባባል ራስህን ትልቅ አደርገህ አታስብ። ትዕቢተኛ አትሁን። ሁሉን አዋቂ አትሁን!

## 7. ቅር የሚያሰኙ እረኞች ምንም ስለማያውቁት ነገር ይከራከራሉ፤ ራሳቸውንም ይከላከላሉ፡፡

"ሳሙኤልም ሳኦልን፦ ቆይ፥ እግዚአብሔር ዛሬ ሌሊት የነገረኝን ልንገርህ አለው። እርሱም፦ ተናገር አለው። ሳሙኤልም አለ። በዓይንህ ምንም ታናሽ ብትሆን ለእስራኤል ነገዶች አለቃ አልሆንህምን? እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ንጉሥ ትሆን ዘንድ ቀባህ።"

1ኛ ሳሙኤል 15፡ 16-17

አለመረዳት፣ አለመስማማት፣ የነገሮችን ጭብጥ አለማወቅ፣ አለማፍራት፣ አለማመን፣ እጅ አለመስጠት፣ አለመጽናት የከባድ መንፈሳዊ በሽታ ምልክቶች ናቸው፡፡ ሳዖል በልቡ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ነበር፤ አለመታዘዙ ምልክት ብቻ ነበር፡፡ ሳዖል በእርግጥም በአመፅ ላይ ነበር፡፡ ሳዖል የነበረበት መንፈሳዊ ሁኔታ አለመታዘዝ፣ አመፅ እና ጥንቆላ ተብሎ ተገለጾአል! ምንም ከማይገባቸውና ሁልጊዜ ከመሪያቸው አመለካከት ጋር ከማይስማሙ ሰዎች ተጠንቀቅ፡፡ መረጃ እየተገኘባቸው ስህተታቸውን ከማያምኑ ሰዎች ተጠንቀቅ፡፡ ስለ አንድ ጉዳይ እነርሱን ለማስረዳት ብዙ ሰዓታትን እንድታጠፋ ከሚያደርጉህ ሰዎች ተጠንቀቅ፡፡ ስለማይለወጡ ሰዎች ተጠንቀቅ፡፡ አደገኛ ቅር የሚያሰኙ ሰዎች ምንም ሊገባቸው አይችሉም፣ ስህተታቸውን ሊያምኑ አይችሉም፣ ምንግዜም አይረዱም፤ በጄ አይሉም፤ ግትሮች ናቸው፤ ጎንበስ አይሉም፤ አይቀበሉም፤ ከሌሎች ጋር አብረው መንገዝ አይችሉም፣ ፈጽሞ አይለወጡም፡፡

## 8. ቅር የሚያሰኝ እረኛ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚታዩ ችግሮች ሌሎችን ይወቅሳል፡፡

"ሕዝቡ ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር በጌልገላ ይሠዉ ዘንድ ከእርሙ የተመረጡትን በጎችንና በሬዎችን ከምርኮው ወሰዱ አለው።"

1ኛ ሳሙኤል 15፡21

መልካም እረኛ ጉባኤው ስለአለመስፋቱ ራሱን ተጠያቂ ያደርጋል፡፡ ‹‹ሳዖል መሰል›› ሚሲዮናዊ ስለተላከበት ተልዕኮ ብዙ ችግር ያወራል፡፡ የተላከበትን አገር ሰዎች ችግር ፈጣሪዎች አድርጎ ነው የሚያያቸው፡፡ የተላኩበትን አገር ሰዎች ጋጠ ወጦች፣ ክፉዎችና ኋላቀር አድርጎ በመግለጽ ስማቸውን ያጠፋል፡፡

ያላወቀው ነገር ቢኖር በዓለም ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ ጋጠ ወጦች፣ ክፉዎችና ኋላ ቀር መሆናቸውን ነው። ክርስቶስ ወደ እነርሱ የላከን ለዚህ ነው። እግዚአብሔር ሚሲዮናዊ አድርጎ የላከን ሰዎች እርዳታ ስለሚያስፈልጋቸው ነው።

## 9. ቅር የሚያሰኙ እረኞች አመጸኛ ልብ ያላቸው ናቸው።

በግልጽ አመፀኞች ላይመስሉ ይችላሉ። እውነታው ግን አመጸኞች መሆናቸው ነው። አለመታዘዝ፣ በሙሉ ልብ ለመከተል አለመቻል፣ በሌሎች ሰዎች ላይ ማሳበብ፣ ራስን ዝቅ አለማድረግ የአመጽ ምልክቶች ናቸው።

> "ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፥ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ አለ።"
>
> 1ኛ ሳሙኤል 15፡23

## 10. ተስፋ አስቆራጭ መጋቢዎች አገልግሎታቸው የጠንቋዮች አይነት አገልግሎት ነው።

> "ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፥ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ አለ።"
>
> 1ኛ ሳሙኤል 15፡23

ጥንቆላ ከመንፈስ ቅዱስ ባልሆነ ኃይል መጠቀም ነው። ጥንቆላ የተለያዩ ዓላማዎችን ለማስፈጸም ሌሎች አማራጭ ኃይሎችን ይጠቀማል። ሳያልን መሰል እረኞች ከአንድ ትልቅ ቡድን ውስጥ የራሳቸውን ተከታዮች እንደሚፈጥሩ እንደ ጠንቋዮች ናቸው። አገልግሎቱ መሪው ካስቀመጠው አቅጣጫ በተቃራኒ እንዲሄድ ያደርጋሉ። እልኸኞችና የማይታዘዙ ስለሆኑ ከትልቁ ቡድን ውስጥ የራሳቸውን ተከታዮች ያፈራሉ።

## 11. ቅር የሚያሰኙ እረኞች ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን ያፍራሉ።

> "ሳኦልም ሳሙኤልን፦ ሕዝቡን ስለ ፈራሁ፥ ቃላቸውንም ስለ ሰማሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝና የአንተን ቃል በመተላለፍ በድያለሁ።"
>
> 1ኛ ሳሙኤል 15፡24

ሳያልን መሰል እረኛ እንደ ፖለቲከኛ ነው። ሰዎች የሚያስቡት ነገር በጣም ያሳስበዋል። በአገልግሎትህ ስለእግዚአብሔር ሀሳብ ይበልጥ መቅርቀር አለብህ። እውነተኛን አገልግሎት ከተሳሳተ አገልግሎት የሚለይ አንድ የተለየ ነገር ቢኖር ይህ ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን የመፍራት ጉዳይ ነው። ሰው የምትፈራ እረኛ ከሆንክ ስብከትህ በሰዎች ሁኔታ ላይ የተመሰረተና ውሳኔህ የሚያወላውል ይሆናል። ሰዎችን መፍራትህ በቀነሰ መጠን አገልግሎትህ እያደገ ይመጣል። የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ያለመፍራት ምሳሌነቱ « ከሰውክብርንአልቀበልም» (ዮሐንስ 5:4) ብሎ በተናገረው ቃል ውስጥ በጉልህ ይታያል።

በአገልግሎት ረዳት መጋቢዎችህን መፍራት የለብህም፣የሌሎች አጥቢያዎች መጋቢዎችህን መፍራት የለብህም። በቤተክርስቲያን ያሉ ሀብታም ሰዎችን መፍራት የለብህም። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ድሆችን መፍራት የለብህም። በቤተክርስቲያን የንግዱን ማሕበረሰብ መፍራት የለብህም። በቤተክርስቲያን ያሉ የፖለቲካ ሰዎችን መፍራት የለብህም። ባለቤትህን መፍራት የለብህም። ከእነዚህ ፍርሀቶች በአንዱ በተያዝክ ጊዜ የአገልግሎትህን ሥልጣን እና በረከትን ታጣለህ።

ሰዎችን መፍራት እነርሱን ከእግዚአብሔር በላይ ማክበር ማለት ነው። ልክ ይህን ስታደርግ በአገልግሎት ትዋረዳለህ። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈሪሳዊያንን አልፈራም። ኢየሱስ ክርስቶስ ረዳት አገልጋዮቹን አልፈራም፣ ሀብታሞች አልፈራም፣ እንዲያውም ሁሉን ሸጣችሁ ተከተሉኝ ነው ያላቸው። በእርግጥም ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን የማይፈራ ታማኝ እረኛ ሁነኛ ምሳሌ ነው።

## 12. ቅር የሚያሰኙ እረኞች እግዚአብሔርን በሚያስደስቱ ነገሮች ደስተኞች አይደሉም።

**ሳሙኤልም በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ፥ መታዘዝ ከመሥዋዕት፥ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል።"**

**1ኛ ሳሙኤል 15:22**

ይህ የሚሆነው ሳያል መሳይ አረኞች እግዚአብሔርን በሚገባ ስለማያውቁት ነው። አንድን ሰው በምታውቀው ጊዜ ምን እንደሚወድና ምን እንደሚጠላ ታውቃለህ። ሁሉን ቻይ ጌታ ልናቀርብለት ከምንችለው ከየትኛውም መስዋዕት ይልቅ መታዘዝን እንደሚወድ ግልጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እኛ የተፈጠርነው ለእግዚአብሔር ደስታ እንደሆነ ያስተምረናል። ስለሆነም የምንኖረው እርሱን ለማስደሰት መሆን አለበት። ብዙ ሰዎች የቅስና ምልክት በአንገታቸው ላይ ያጠልቃሉ፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን አያውቁትም። እርሱን የሚያስደስተው ምን እንደሆነ አያውቁም።

## 13. ቅር የሚያሰኙ እረኞች በእግዚአብሔር የተናቁ ናቸው።

> "ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፥ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ አለ።"
>
> 1ኛ ሳሙኤል 15፡23

ከላይ የገለጽኳቸውን ባህሪያት የሚያሳዩ መጋቢዎች መጨረሻ በእግዚአብሔር መናቅ ነው። አገልግሎትህ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ጥረት ማድረግ አለብህ። በምታደርገው እግዚአብሔር መደሰት አለበት። አለበለዚያ የምታደርገው ሁሉ ዋጋ ቢስ ነው።

## ምዕራፍ 32

# የእረኞች ዕድገት ሃያ ሁለት ደረጃዎች

እረኛውና ብላቴናው ዳዊት በሳሙኤል ተቀብቶ የእስራኤል ንጉሥ ሆነ። አነስተኛ የበግ መንጋ ከማገድ ታዋቂ ወደሆነበት የእስራኤል ህዝብ እረኛ ወደ መሆን ተሸጋገረ። መዝሙር 23 የዳዊትን እውነተኛ የእረኝነት ህይወት የሚያሳይ ነው።

ዳዊት የተቀባ የእስራኤል እረኛ የሆነው እንዴት ነው? በርካታ ዓመታትን በፈጀ ወለም ዘለም ጥንቃቄ በሞላበት ሂደት ውስጥ አልፎ ነው። በእግዚአብሔር ተመርጦና በሳሙኤል ተቀብቶ የጀመረው ጉዞ የእስራኤል ንጉሥ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ የቀጠለ ነበር። በዚህ ምዕራፍ ዳዊት ዝነኛ የእስራኤል እረኛ ለመሆን ያለፈባቸውን ደረጃዎች ላሳያችሁ እፈልጋለሁ። እነዚህ ደረጃዎች ዋና ቁምነገሮች ናቸው፤ ምክንያቱም አንተም በጌታ የተቀባህ አገልጋይ ለመሆን በምታደርገው ጉዞ ላይ የሚከሰቱ ናቸው። እነዚህን ደረጃዎች በሚገባ አጥናና በእግዚአብሔር የተወደደውንና የእስራኤል ተወዳጅ መዝሙረኛ የሆነውን የንጉሥ ዳዊትን ምሳሌ ተከተል።

1. **ከሌሎች ወንድሞችና እህቶች መካከል በመመረጥህ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት ተቀበል። ዳዊት ከወንድሞቹ መካከል እንደተጠራ አንተም ከቤተሰብህ መሀከል ትጠራለህ።**

   **"ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወንድሞቹ መካከል ቀባው። የእግዚአብሔርም መንፈስ ከዚያ ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ በኃይል መጣ። ሳሙኤልም ተነሥቶ ወደ አርማቴም ሄደ።"**

   **1ኛ ሳሙኤል 16:13**

2. **በቤተክርስቲያን ውስጥ የመዘመርና የሙዚቃ መሳሪያ የመጫወት ክህሎት አዳብር። ዳዊት በገና የመደርደር ችሎታ እንደነበረው ሁሉ አንተም እንዲህ ያለውን ለቤተክርስቲያን የሚጠቅም ጥበብ መማር አለብህ።**

ከብላቴኖቹም አንዱ መልሶ፡- እነሆ፥ መልካም አድርጎ በገና የሚመታ የቤተ ልሔማዊውን የእሴይን ልጅ አይቻለሁ እርሱም ጽኑዕ ኃያል ነው፥ በነገርም ብልህ፥ መልኩም ያማረ ነው፥ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነው አለ።

1ኛ ሳሙኤል 16፡18

3. በጸሎትና የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት እንደ ዳዊት በመንፈስ የጠነከርክ ሁን፡፡

"ከብላቴኖቹም አንዱ መልሶ፡- እነሆ፥ መልካም አድርጎ በገና የሚመታ የቤተ ልሔማዊውን የእሴይን ልጅ አይቻለሁ እርሱም ጽኑዕ ኃያል ነው፥ በነገርም ብልህ፥ መልኩም ያማረ ነው፥ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነው አለ።"

1ኛ ሳሙኤል 16፡18

4. እንደ ዳዊት አንተም የላቀ ልምድ ያላቸውን የሽማግሌዎችን ምክር በመስማት ጥበብን ተለማመድ፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ ወጣቶች የሚያደርጉት ነገር ነው፡፡

"ከብላቴኖቹም አንዱ መልሶ፡- እነሆ፥ መልካም አድርጎ በገና የሚመታ የቤተ ልሔማዊውን የእሴይን ልጅ አይቻለሁ እርሱም ጽኑዕ ኃያል ነው፥ በነገርም ብልህ፥ መልኩም ያማረ ነው፥ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነው አለ።"

1ኛ ሳሙኤል 16፡18

5. ዳዊት የሳዖል ጋሻ ጃግሬ እንደነበረ ሁሉ አንተም ከአንተ ቀደም ያለውን አገልጋይ ልታገለግል ይገባሀል፡፡

"ዳዊትም ወደ ሳኦል መጣ፥ በፊቱም ቆመ እጅግም ወደደው፥ ለእርሱም ጋሻ ጃግሬው ሆነ።"

1ኛ ሳሙኤል 16፡21

6. በምታገለግለው በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ማግኘትህን አረጋግጥ፡፡ አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሰው በሚያገለግሉበት ጊዜ በፊቱ ሞገስ ያጣሉ፡፡

"ዳዊትም ወደ ሳኦል መጣ፥ በፊቱም ቆመ እጅግም ወደደው፥ ለእርሱም ጋሻ ጃግሬው ሆነ።"

1ኛ ሳሙኤል 16፡21

7. ዳዊት የታወቀ የቤተ መንግሥት ሙዚቀኛ እንደነበረ ሁሉ በአገልግሎትህ የተመሰከረለት አገልጋይ ሁን፡፡

እንዲህም ሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በሆነ ጊዜ ዳዊት በገና ይዞ በእጁ ይመታ ነበር ሳኦልንም ደስ ያሰኘው ያሳርፈውም ነበር፥ ክፉ መንፈስም ከእርሱ ይርቅ ነበር።

1ኛ ሳሙኤል 16፡23

## 8. ለበጎችህ በመጸለይ፣ በመጎብኘት፣ በማማከርና ከእነርሱ ጋር ግንኙነትን በመፍጠር የእረኝነት ተግባርህን ፈጽም።

"ዳዊትም ማልዶ ተነሣ፥ በጎቹንም ለጠባቂ ተወ፥ እሴይም ያዘዘውን ይዞ ሄደ ጭፍራውም ተሰልፎ ሲወጣ ለሰልፍም ሲጮኽ በሰረገሎች ወደ ተከበበው ሰፈር መጣ።"

1ኛ ሳሙኤል 17፡20

## 9. ዳዊት እንዳደረገው አንበሣንና ድቡን በመግደል ደፋርና ኃላፊነት የሚሰማው ሁን።

ዳዊትም ሳኦልን አለው። እኔ ባሪያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር፥ ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር።

በኋላውም እከተለውና እመታው ነበር፥ ከአፉም አስጥለው ነበር በተነሣብኝም ጊዜ ጕሮሮውን ይዤ እመታውና እገድለው ነበር።

1ኛ ሳሙኤል 17፡34-35

## 10. ድካምህን የምትረዳ መሆንህን አሳይ። ይህ ብዙዎች የሌላቸው ነገር ነው።

"ሳኦልም ዳዊትን የገዛ ራሱን ልብስ አለበሰው፥ በራሱም ላይ የናስ ቍር ደፋለት፥ ጥሩርም አለበሰው። ዳዊትም ሰይፉን በልብሱ ላይ ታጠቀ፥ ገናም አልፈተነውምና መሄድ ሞከረ።ዳዊትም ሳኦልን፡-አልፈተንሁትምና እንዲህ ብዬ መሄድ አልችልም አለው። ዳዊትም አወለቀ። በትሩንም በእጁ ወሰደ፥ከወንዝም አምስት ድብልብል ድንጋዮችን መረጠ፥በእረኛ ኮረጆውም በኪሱ ከተታቸው ወንጭፍም በእጁ ነበረ ወደ ፍልስጥኤማዊውም ቀረበ።"

1ኛ ሳሙኤል 17፡38-40

## 11. ካሳለፍነው ነገር ትምህርት መቅሰምህን ከልምድ ባገኘኸው ነገር በመጠቀም አሳይ።

ሳኦልም ዳዊትን የገዛ ራሱን ልብስ አለበሰው፥ በራሱም ላይ የናስ ቍር ደፋለት፥ ጥሩርም አለበሰው። ዳዊትም ሰይፉን በልብሱ ላይ ታጠቀ፥ ገናም አልፈተነውምና መሄድ ሞከረ። ዳዊትም ሳኦልን፡- አልፈተንሁትምና እንዲህ ብዬ መሄድ አልችልም

አለው። ዳዊትም አወለቀ። በትሩንም በእጁ ወሰደ፥ ከወንዝም አምስት ድብልብል ድንጋዮችን መረጠ፥ በእረኛ ኮረጆውም በኪሱ ከተታቸው ወንጭፍም በእጁ ነበረ ወደ ፍልስጥኤማዊውም ቀረበ።

1ኛ ሳሙኤል 17፡38-40

## 12. ኀልያድን በጌታ ስም በመግጠም ለእግዚአብሔርና ለህዝቡ ያለህን ፍቅር አሳይ።

"ዳዊትም ፍልስጥኤማዊውን አለው። አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርኸው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ። እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል እመታህማለሁ፥ ራስህንም ከአንተ አነሣዋለሁ የፍልስጥኤማውያንንም ሠራዊት ሬሶች ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት ዛሬ እሰጣለሁ። ይኸውም ምድር ሁሉ በእስራኤል ዘንድ አምላክ እንዳለ ታውቅ ዘንድ ይህም ጉባኤ ሁሉ እግዚአብሔር በሰይፍና በጦር የሚያድን እንዳይደል ያውቅ ዘንድ ነው። ሰልፉ ለእግዚአብሔር ነውና እናንተንም በእጃችን አሳልፎ ይሰጣል።"

1ኛ ሳሙኤል 17፡45-47

## 13. ዳዊት ከዮናታን ጋር የቅርብ ግንኙነት እንደነበረው ሁሉ አንተም ከሌሎች ሰዎችና ከአገልግሎት አጋሮችህ ጋር የቅርብ ግንኙነት የመፍጠር ብቃትህን በተግባር አሳይ።

"ዳዊትም ለሳኦል መናገሩን በፈጸመ ጊዜ የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች፥ ዮናታንም እንደ ነፍሱ ወደደው። በዚያም ቀን ሳኦል ወሰደው፥ ወደ አባቱም ቤት ይመልሰው ዘንድ አልተወውም። ዮናታንም እንደ ነፍሱ ስለ ወደደው ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። ዮናታንም የለበሰውን ካባ አውልቆ እርሱንና ልብሱን ሰይፉንም ሸለመው። ዮናታንም የለበሰውን ካባ አውልቆ እርሱንና ልብሱን ሰይፉንም ቀስቱንም መታጠቂያውንም ለዳዊት ሸለመው።"

1ኛ ሳሙኤል 18፡1-4

## 14. ዳዊት ከዮናታን ጋር የሕይወት ዘመን እንዳደረገ ሁሉ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦችህ ጋር የሚጸና ቃል ኪዳን መመሥረት መቻልህን በተግባር አሳይ።

"ዮናታንም እንደ ነፍሱ ስለ ወደደው ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን አደረገ።"

1ኛ ሳሙኤል 18፡3

## 15. ቀልፍ ኃላፊነቶች ላይ በምትመደብበት ጊዜ በጥበብ በመመላለስ ሥልጣንና የሥራ ሹመትን በአግባቡ የመያዝ ብቃትህን አሳይ

"ዮናታንም እንደ ነፍሱ ስለ ወደደው ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን አደረገ።ዳዊትም ሳኦል ወደ ሰደደው ሁሉ ይሄድ ነበር፥ አስተውሎም ያደርግ ነበር ሳኦልም በጦረኞች ላይ ሾመው ይህም በሕዝብ ሁሉ ዓይን እና በሳኦል ባሪያዎች ዓይን መልካም ነበረ።"

1ኛ ሳሙኤል 18:5

## 16. ዳዊት እንዳደረገው ከምዕመናን ለአገልግሎት ለመሾም የሚጠቅምህን ምስክርነት አሳድግ::

እንዲህም ሆነ ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ገድሎ በተመለሰ ጊዜ፥ እየዘመሩና እየዘፈኑ እልልም እያሉ ከበሮና እታሞ ይዘው ንጉሡን ሳኦልን ሊቀበሉ ሴቶች ከእስራኤል ከተሞች ሁሉ ወጡ።

"ሴቶችም። ሳኦል ሺህ፥ ዳዊትም እልፍ ገደለ እያሉ እየተቀባበሉ ይዘፍኑ ነበር።"

1ኛ ሳሙኤል 18:6-7

## 17. እንደ ዳዊት የቀደሙትን አገልጋዮች ቅናት ተቋቋም::

"እንዲህም ሆነ ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ገድሎ በተመለሰ ጊዜ፥ እየዘመሩና እየዘፈኑ እልልም እያሉ ከበሮና እታሞ ይዘው ንጉሡን ሳኦልን ሊቀበሉ ሴቶች ከእስራኤል ከተሞች ሁሉ ወጡ። ሴቶችም። ሳኦል ሺህ፥ ዳዊትም እልፍ ገደለ እያሉ እየተቀባበሉ ይዘፍኑ ነበር። ሳኦልም እጅግ ተቈጣ፥ ይህም ነገር አስከፋው እርሱም:- ለዳዊት እልፍ ሰጡት፥ ለእኔ ግን ሺህ ብቻ ሰጡኝ ከመንግሥት በቀር ምን ቀረበት? አለ። ከዚያም ቀን ጀምሮ ሳኦል ዳዊትን ተመቅኝቶ ተመለከተው።"

1ኛ ሳሙኤል 18:6-9

## 18. ዳዊት እንዳደረገ በሥልጣን ላይ ያለ ሰውን ጽኑ ቁጣ በፅናት እለፈው::

"በነጋውም ሳኦልን ክፉ መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያዘው፥ በቤቱም ውስጥ ትንቢት ተናገረ። ዳዊትም በየቀኑ ያደርግ እንደ ነበረ በእጁ በገና ይመታ ነበር። ሳኦልም ጦሩን በእጁ ይዞ ነበር። ሳኦልም። ዳዊትን ከግንቡ ጋር አጣብቄ እመታዋለሁ ብሎ ጦሩን ወረወረ። ዳዊትም ሁለት ጊዜ ከፊቱ ዘወር አለ።"

1ኛ ሳሙኤል 18:10-11

## 19. ዳዊት እንዳደረገ አንተን ከአገልግሎትህ ለማንሳት የሚደረገውን መከራ ሁሉ ተቋቋም::

"በነጋውም ሳኦልን ከፉ መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያዘው፥ በቤቱም ውስጥ ትንቢት ተናገረ። ዳዊትም በየቀኑ ያደርግ እንደ ነበረ በእጁ በገና ይመታ ነበር። ሳኦልም ጦሩን በእጁ ይዞ ነበር። ሳኦልም። ዳዊትን ከግንቡ ጋር አጣብቄ እመታዋለሁ ብሎ ጦሩን ወረወረ። ዳዊትም ሁለት ጊዜ ከፊቱ ዘወር አለ።"

1ኛ ሳሙኤል 18፡10-11

## 20. እንድትተቻቸው ከሚያነሳሱህ የእግዚአብሔር ሰዎች ዘወር በማለት ረገድ የላቀ ጥበብ አሳይ።

"ዮናታንም። አባቴ ሳኦል ሊገድልህ ፈልጎአል አሁን እንግዲህ ለነገው ተጠንቀቀህ ተሸሸግ፥ በሰውርም ተቀመጥ"

1ኛ ሳሙኤል 19፡2

## 21. ዳዊት ወደ ሳሙኤል ይሮጥ እንደነበረ ለማረፍ፣ ጥበቃ ለማግኘት፣ ለመቀባት፣ ምሪትን ለመቀበል፣ እና ለመታደስ ወደሚያስችሉ አመቺ ቦታዎች ጊዜ የመውሰድ ጥበብ ይኑርህ።

"ዳዊትም ሸሽቶ አመለጠ፥ ወደ አርማቴምም ወደ ሳሙኤል መጣ፥ ሳኦልም ያደረገበትን ሁሉ ነገረው እርሱና ሳሙኤልም ሄዱ በነዋትዘራማም ተቀመጡ። ሳኦልም። ዳዊት፥ እነሆ፥ በአርማቴም አገር በነዋትዘራማ ተቀምጦአል የሚል ወሬ ሰማ። ሳኦልም ዳዊትን ያመጡት ዘንድ መልእክተኞችን ሰደደ የነቢያት ጉባኤ ትንቢት ሲናገሩ፥ ሳሙኤልም አለቃቸው ሆኖ ሲቆም ባዩ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በሳኦል መልእክተኞች ላይ ወረደ፥ እነርሱም ትንቢት ይናገሩ ጀምር።"

1ኛ ሳሙኤል 19፡18-20

## 22. ዳዊት ለብዙ አመታት ኮብላይ መሆኑን እንደተቀበለ ሁሉ አድራሻህን የሚያስለውጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከመጣ ተቀበለው።

"ዮናታንም ደግሞ። ቶሎ ፍጠን፥ አትቆይ ብሎ ወደ ብላቴናው ጮኸ የዮናታንም ብላቴና ፍላጻዎቹን ሰብስቦ ወደ ጌታው መጣ። ዮናታንና ዳዊት ብቻ ነገሩን ያውቁ ነበር እንጂ ብላቴናው ምንም አያውቅም ነበር። ዮናታንም መሣርያውን ለብላቴናው ሰጥቶ። ወደ ከተማ ውሰድ አለው። ብላቴናውም በሄደ ጊዜ ዳዊት ከስፍራው በደቡብ አጠገብ ተነሣ፥ በምድርም ላይ በግምባሩ ተደፋ፥ ሦስት ጊዜም ለሰላምታ ሰገደ እየተላቀሱም እርስ በእርሳቸው ተሳሳሙ፥ ይልቁንም ዳዊት እጅግ አለቀሰ። ዮናታንም ዳዊትን፦ በደኅና ሂድ እነሆ፥ እኛ ሁለታችን በእኔና በአንተ፥ በዘሬና በዘርህ መካከል ለዘላለም እግዚአብሔር ይሁን ብለን በእግዚአብሔር ስም ተማምለናል አለው። ዳዊትም ተነሥቶ ሄደ ዮናታንም ወደ ከተማ ገባ።"

1ኛ ሳሙኤል 20፡ 35-42

## ምዕራፍ 33

# መንፈሳዊ ልጅ ወደ እረኝነት የሚያድግበት መንገድ

"ስለዚህ የምወደውንና የታመነውን በጌታ ልጄ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልኬላችኋለሁ፥ እኔም በየስፍራው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደማስተምር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚሆነውን መንገዴን እርሱ ያሳስባችኋል።"

1ኛ ቆሮንቶስ 4፡17

ጢሞቴዎስ ከመንፈሳዊ ልጅነት ወደ መጋቢነት የማደግ ጉልህ ማሳያ ነው፡፡ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በእንደዚያ አይነት ሁኔታ እንዲጽፍ ሥልጣን የሰጠው ጢሞቴዎስ የጳውሎስ መንፈሳዊ ልጁ በመሆኑ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ምንና እንዴት ማድረግ እንዳለበት በነጻነት ይነግረው ነበር፡፡ልጅህን በምትናገርበት ጊዜ በልብህ ያለውን ሁሉ ያለፍርሀት ትናገራለህ፡፡

ጳውሎስ መንፈሳዊ ልጁን በነፃነት የመከረበት የ1ኛ እና የ2ኛ ጢሞቴዎስ መጻህፍትን ማግኘታችን ታላቅ በረከት ነው፡፡ የጢሞቴዎስ መንፈሳዊ ልጅነት ከጳውሎስ ውስጥ ይፈስ ለነበረው ምሪትና መልካም ተጽዕኖ ክፍት እንዲሆን አደረገው፡፡ ጢሞቴዎስ ለጳውሎስ አባትነትና ትምህርት ያለውን ፍላጎት ሳያሳይ አልቀረም፡፡ የተቻለውን ያህል እንዲያስተምረው ጢሞቴዎስ ጳውሎስን ሳያነሳሳውም አልቀረም፡፡ ጢሞቴዎስ ለመማር ሳይጓጓ አልቀረም፡፡ ይህም ደግሞ ጳውሎስ ምን መስበክ እንዳለበት ለጢሞቴዎስ እስከመንገር ድረስ ዝርዝር ምክር እንዲሰጠው አነሳሳው፡፡ (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡2)

ጳውሎስ ያሳደጋቸው ነገር ግን ለጢሞቴዎስ የነገረውን ሁሉ ያልነገራቸው ሌሎች ሰዎች አይጠፉም፡፡ ለምሳሌ ዲዮጥራጦስ የሐዋሪያው ዮሐንስን ትምህርት ስላለመቀበሉ ዮሐንስ በ3ኛው መልዕክት ላይ ጽፎ እናገኛለን "ወደ ቤተክርስቲያን ጻፍሁ፤ዳሩ ግን ዋናቸው ሊሆን የሚወድ ዲዮጥራጢስ አይቀበለንም፡፡" (3ኛ ዮሐንስ 9)

አገልጋይ የሐዋሪያውን ምክር መስማት ሲያቆም ራሱን ለፍርድ ያጋልጣል። አዲስ ቅባት በመቀበል ፈንታ ፍርድን ይቀበላል፤ ‹‹የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፤እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል።›› (ዮሐንስ 12፡48)

አስፈላጊ የሆኑ የልጅነት ባህሪያትን ማዳበር እጅግ ጠቃሚ ነው። ይህ ለአባት በረከት ክፍት ያደርግሀል። ስለአንተ የሐዋሪያውን ቅባት ያንቀሳቅሰዋል ስጦታውንም ያነሳሳዋል። እንደልጅ የመገዛትን ባህሪ አዳብር። ለአስደናቂ በረከት ያበቃሀል።

## 1. እንደ ልጅ የተማሪነት መንፈስ ማሳየት አለብሀ።

ለመማር የተዘጋጀህ ስትሆን የማታውቀውን ብዙ ነገር ትማራለህ። መምህር ‹‹ሁሉን አውቃለሁ›› የሚልን ስሜት በቀላሉ ለይቶ ያውቃል። መምህራን ማን ለመማር ፍላጎት እንደሌለው እና እንደሚቃወም በቀላሉ ይረዳሉ።

> "አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤"
>
> 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡14

## 2. ከሌሎች ጋር የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) የልጅነት መንፈስ አሳይ።

> "እንደ እርሱ ያለ፥ ስለ ኑሮአችሁ በቅንነት የሚጨነቅ፥ ማንም የለኝምና፤"
>
> ፊልጵስዩስ 2፡20

የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) ማለት፡-

1. የሚዛመድ መንፈስ
2. የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) መንፈስ ከመንፈሳዊ አባቱ ጋር ተመሳሳይ መንፈስ ያለው ማለት ነው።
3. የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) ልጅ ከአባቱ ጋር ተመሳሳይ አመለካከት አለው።
4. የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) ልጅ ከአባቱ ጋር ይግባባል።
5. የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) ልጅ የአባቱን ችግር ይረዳል።

6. የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) ልጅ የአባቱ ጉዳይ ይገደዋል።
7. የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) ልጅ ተስማሚ እንጂ ተከራካሪ አይደለም።
8. የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) ልጅ ከአባቱ ራዕይ ጋር አብሮ የሚተም ነው።
9. የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) ልጅ ወዳጅና ዝምድና አዋቂ ነው።
10. የሚጣጣም (አብሮ የሚፈስ) ልጅ መልካም አጋር ነው። ይሕ ማለት በጉዞህ አጋር ሊሆንህ ይችላል። አንዳንድ ሰዎች አጠገብህ ሲሆኑ መልካም ነገር አይሰማህም። ስለምንም ነገር አንዳች አይናገሩም። ነገራቸው ሁሉ በውስጥ ነው።

## 3. የእውነተኛ ልጅ አባትን የመንከባከብ አቋም ይኑርህ።

የልጅ ዓይን ለአባቱ ባለው ፍቅርና እንክብካቤ የተሞላ ነው።

"እንደ እርሱ ያለ፥ ስለኑሮአችሁ በቅንነት የሚጨነቅ፥ ማንም የለኝምና፤"

ፊልጵስዩስ 2:20

## 4. ልጅ ያለውን የአገልጋይነት መንፈስ ማሳየት አለብህ።

"ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና፥ የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም። ነገር ግን ልጅ ለአባቱ እንደሚያገለግል ከእኔ ጋር ሆኖ ለወንጌል እንደ አገለገለ መፈተኑን ታውቃላችሁ።"

ፊልጵስዩስ 2:21-22

## 5. እንደ ልጅ ታማኝነትን ማሳየት አለብህ።

ልጅ በአስቸጋሪ ሁናቴ ውስጥ እንኳን የታመነ ነው። ልጅነትህን የሚያረጋግጠው በአስቸጋሪ ጊዜ የምታሳየው እምነት ነው።

ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና፥ የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም። ነገር ግን ልጅ ለአባቱ እንደሚያገለግል ከእኔ ጋር ሆኖ ለወንጌል እንደ አገለገለ መፈተኑን ታውቃላችሁ።

ፊልጵስዩስ 2:21-22

## 6. ልጅነትህን የሚመዝንን ፈተና ማለፍ አለብህ።

በጊዜ ውስጥ እውነተኛ ልጅ መሆንህን የሚፈትኑ የተለያዩ ሁኔታዎች ይከሰታሉ። ግልፅ፣ ትሑት እና እሺ ባይ መሆንህ ይፈተናል። እስከመጨረሻው የመከተል ብቃትህ ይፈተናል።

"ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና፥ የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም። ነገር ግን ልጅ ለአባቱ እንደሚያገለግል ከእኔ ጋር ሆኖ ለወንጌል እንደ አገለገለ መፈተኑን ታውቃላችሁ።"

ፊልጵስዩስ 2፡21-22

## 7. እንደ ልጅ ሁልጊዜ እንደ ህጻን መመላለስ አለብህ።

ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና፥ የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም። ነገር ግን ልጅ ለአባቱ እንደሚያገለግል ከእኔ ጋር ሆኖ ለወንጌል እንደ አገለገለ መፈተኑን ታውቃላችሁ።

ፊልጵስዩስ 2፡21-22

## 8. የአባትህን ሥራ ቀጣይነት በማረጋገጥ ልጅነትህን ማስመስከር አለብህ።

"ስለ እምነታችሁም እንዲያጸናችሁና እንዲመክራችሁ ወንድማችንን የእግዚአብሔርንም አገልጋይ ከእኛ ጋርም አብሮ በክርስቶስ ወንጌል የሚሠራውን ጢሞቴዎስን ላክነው፤"

1ኛ ተሰሎንቄ 3፡2

መንፈሳዊ ልጅ አባቱ የጀመረው መጽናቱን ያረጋግጣል። ጳውሎስ ለቤተክርስቲያን ተከላ ረጃጅም ጉዞዎችን አድርጓል። የጠፋትን ለመታደግና ቤተክርስቲያኖችን ለመትከል በወቅቱ በሚታወቀው ዓለም ዙሪያ ተዘዋውሯል። መንፈሳዊ ልጁም የአባቱን ሥራ ለማስቀጠል ተመሳሳይ ርቀት ለመሄድ ተዘጋጅቶ ነበር። እውነተኛ ልጅ ማንኛውም አባቱ የጀመረውን ሥራ እድገት ቀጣይነት ማየትን ይናፍቃል። እውነተኛ ያልሆኑ ልጆች በአባታቸው ራዕይና የእድሜ ዘመን ሥራ ላይ ስለሚሆነው ነገር ምንም ደንታ የላቸውም። ጢሞቴዎስ በጳውሎስ የተጀመረውን ሥራ ለማስቀጠል እንዴት ወደፊት እንደቀጠለ አስተውል።

## 9. የአባትህ ቃል መጠበቁንና ሰዎች ለዚያ ቃል መታዘዛቸውን በማረጋገጥ ልጅነትህን ማስመስከር አለብህ።

መስራቹ ወይም አባት ከሞተ በኋላ የተናገረውንና ያደረገውን ለማጣመም የሚሞክሩ ሰዎች ይነሳሉ። እውነተኛ ልጅ የአባቱን

አስተምህሮና እምነት ጠብቆ ለማቆየት ይፋለማል። ዋና ትኩረቱ መጽሐፍ ለመጻፍ ሳይሆን የተጻፉ መጽሐፍት ትምህርት እንዲሰጡ እና ሰዎች እንዲረዱአቸው ማድረግ ነው።

"አንዳንዶች ልዩ ትምህርትን እንዳያስተምሩና ወደ ተረት መጨረሻም ወደሌለው ወደ ትውልዶች ታሪክ እንዳያደምጡ ልታዛቸው በኤፌሶን ትቀመጥ ዘንድ ለመንሁህ!"

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡3

"ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።"

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡2

## 10. በአባትህ የነበረውን ያንኑ ቅናት በማሳየት ልጅነትህን ማስመስከር አለብህ

ቲቶ በተመሳሳይ መሰጠት፣ ትኩረትና ሥልጣን እንዲሰብክ እንደተነገው እናያለን። ልጅ ያልሆነ ሰው አባቱ ያስተማረውን ያንኑ ትምህርት አያስተምርም፤ የሚናገረውንም ነገር በአባቱ መሰጠትና ሥልጣን ልክ አይናገረውም። እውነተኛ ልጆች ያልሆኑ ሰዎች በሥልጣን የሚናገሩት አባታቸው ያስተማራቸው ሳይሆን ሌሎች ጉዳዮች ነው።

"ይህን በሙሉ ሥልጣን ተናገርና ምከር ገሥጽም፤ ማንም አይናቅህ።"

ቲቶ 2፡15

## ምዕራፍ 34

# እረኛ ሊያድግባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች

## 1. እረኞች በውጊያ ችሎታ ማደግ አለባቸው፡፡

አገልግሎት ለእግዚአብሔር የሆነ የከበረ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ወደ አገልግሎት መግባት ወደ ወታደራዊ ዘመቻ እንደመግባት ያህል ነው፡፡ አገልግሎት በጦርነት ውስጥ እንደመካፈል ነው፡፡ በሚጠላህ ጠላትህ እይታ ውስጥ ትገባለህ፡፡ያንተን ብርሀን ማጥፋት ዋና ዓላማቸው በሆነ ርኩሳን መናፍስት የመወያያ አጀንዳ ትሆናለህ፡፡ ውጊያን መማር አለበህ፡፡ ስትዋጋም እንደሚጋባ መዋጋት አለብህ፡፡ ፈጽሞ ተስፋ አትቁረጥ ወይም አታፈግፍግ! ውጊያ በመሆኑ ሙሉ መጽሐፍ ፅፌበታለሁ፡፡

"ጢሞቴዎስ ልጄ ሆይ፥ አስቀድሞ ስለ አንተ እንደ ተነገረው ትንቢት፥ በእርሱ መልካም ጦርነት ትዋጋ ዘንድ ይህችን ትእዛዝ አደራ እሰጥሃለሁ፤"

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡18

## 2. እረኞች በህሊናቸው ማደግ አለባቸው፡፡

"የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው፤"

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡5

ህሊና ስለመልካምና ክፉ የሚያስጠነቅቅህ ከውስጥ የሚሰማህ ዝግ ያለ ድምጽ ነው፡፡ ህሊና የመንፈስ ይሁን ወይም የነፍስ በትክክል መናገር አልችልም፡፡ ነገር ግን የማውቀው ነገር ቢኖር ህሊና ክፉ ነገርን በምታደርግበት ጊዜ የሚወቅስህ ‹‹ከውስጥ›› የሆነ የሚያስጠንቀቂያ ብርሀን መሆኑን ነው፡፡

ንቁ ህሊና አለህ ማለት በውስጥህ ፈጣን የማስጠንቀቂያ ሥሬዓት አለህ ማለት ነው፡፡ ይህን የማስጠንቀቂያ ሥርዓት ችላ ብትል ወደማይነገሩ ችግሮች ትገባለህ፡፡

በቅርቡ በእስያ የተከሰተው የሱናሚ አደጋ ዓለምን በድንጋጤ ከመምታቱም ሌላ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን ለህልፈተ ህይወት

የዳረገ ነበር። ለዚህ የወል እልቂት ምክንያቱ የጥልቅ ባህር ውስጥ የማስጠንቀቂያ ሥርዓት አለመኖሩ ነበር። ከአደጋው በኋላ ግን አደጋን አስቀድሞ የሚያነብና በብዙ ርቀት ላሉ ቢሮዎች መረጃ የሚያቀብል መስመር ዘርግተዋል።

ይህ የሱናሚ ቅድመ ማስጠንቀቂያ መሳሪያ ሊመጣ ከሚችል ግዙፍ የመሬት መናወጥ ለማምለጥ ያግዛል ተብሎ ታምኖበታል። የሱናሚውን አደጋ በተመለከተ ከአምስት ደቂቃ በፊት የማስጠንቀቂያ መረጃ ቢሰጣቸው ኖሮ ምን ያህል ሰው ሊተርፍ እንደሚችል መገመት አያዳግትም። እግዚአብሔር ህሊናን የሰጠን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት እናገኝ ዘንድ ነው።

እንደ የሱናሚ ቅድመ ማስጠንቀቂያ መሳሪያ ህሊና ከሞላ ጎደል ንቃት ሊኖረው ይችላል። ንቃቱ በጨመረ መጠን ራስህን በየደቂቃው ስለ ኃጢአትህ ንስሀ ስትገባና የእግዚአብሔርን ምህረት ስትለምን ታገኘዋለህ። የህሊናህ ንቃት በቀነሰ ቁጥር ደግሞ ንስሀ የምትገባው በጣም ጥቂት በሆኑ ጉዳዮች ነው።

ግትርና ደንዳና ህሊና ካለህ ኃጢአትህን በየጊዜው አትናዘዝም። ደንዳና ህሊና ካለህ ራስህን ሁልጊዜ ጻድቅ አድርገህ ነው የምትቆጥረው። የተደጋገመ ኃጢአት ደንዳና ህሊና እንዲኖረን ያደርጋል። ‹‹በክፉ ሥራ ላይ ፈጥኖ ፍርድ አይፈረድምና ስለዚህ በሰው ልጆች ውስጥ ልባቸው ክፉን ለመሥራት ጠነከረ።›› (መክብብ 8፡11)

> "እምነትና በጎ ሕሊና ይኑርህ፥ አንዳንዶች ሕሊናን ጥለው፥ መርከብ እለ መሪ እንደሚጠፋ፥ በእምነት ነገር ጠፍተዋልና፤ ከእነዚያም፥ እንዳይሳደቡ ይማሩ ዘንድ ለሰይጣን አሳልፌ የሰጠኋቸው፥ ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ ናቸው።"
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡19-20

ከላይ በጥቅሱ ውስጥ እንደምታየው ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ ህሊናቸውን ጥለው በእምነት ነገር ጠፍተዋል። ንቁ የማስጠንቀቂያ ሥርዓት መጣል አደገኛ ነገር ነው። በህይወትህ ሁሉ ንቁ ህሊና ሊኖርህ ያስፈልጋል። ብዙ ጻድቅ ከመሆን፣ ብዙ ይቅርታ ጠያቂ መሆን ይሻላል። ‹‹እጅግ ጻድቅ አትሁን፥ እጅግ ጠቢብም አትሁን፥ እንዳትጠፋ።›› (መክብብ 7፡16)

## 3. እረኞች እግዚአብሔርን በመምሰል ማደግ አለባቸው

"አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል።"

1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡11

መጋቢዎች የበለጠ እግዚአብሔርን ወደመምሰል ማደግ ይገባቸዋል፡፡ ያህዌ እንደ ጽድቅ፣ ቅድስና፣ እምነት፣ ፍቅር፣ ትዕግስት፣እና ጭምትነት ያሉ መልካም ባህሪያትን የተሞላ አምላክ ነው፡፡ እነኚህ ባህሪያት በጣም ጉልበታም ወይም የሚስቡ ላይመስሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በመንፈሳዊ ህይወትህ ልታሳድጋቸው የሚገባህ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡

እግዚአብሔር የልጁን መልክ እንመስል ዘንድ በውስጣችን እየሰራ ነው፡፡ ግባችን ስኬት ወይም ዝና አይደለም፡፡ *የእኛ ግብ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ማደግ ነው፡፡* መጽሐፍ ቅዱስህን በጥንቃቄ አንብብና የተወሰነልህን ግብ ለይተህ እወቅ፡፡

"ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፤"

ሮሜ 8፡29

## 4. እረኞች መንፈሳዊ ነገሮችን መከታተል አለባቸው፡፡

"አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል።"

1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡11

‹‹መከታተል›› የሚለው ቃል *dioko* ከሚል የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ለአንድ ነገር ህይወትን መስጠትና ያንን ነገር በብርቱ መከታተል የሚል ትረጉም ያለው ነው፡፡

ብዙ መጋቢዎች አካላዊና ተፈጥሯዊ ግቦች አሏቸው፡፡ የጸሎት ርዕሶቻቸው ይህን ያመለክታሉ፡፡ እንደ ትህትና፣ ፍቅር፣ እና ቅድስና ላሉ መንፈሳዊ ነገሮች የምንጸልየው አልፎ አልፎ ነው፡፡ በተደጋጋሚ የምንጸልየው ለሚዳሰሱ እንደ ገንዘብ ወይም የቁጥር ብዛት ላሉ ነገሮች ነው፡፡ ጳውሎስ ግን እንደ መንፈሳዊ ጥበብና መገለጥ ለመሳሰሉ መንፈሳዊ ነገሮች እንደጸለየ ትረዳለህ:: (ኤፌሶን 1፡17)

የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲያውቁ ጸለየላቸው (ኤፌሶን 3፡18)፡፡ እነዚህ ረቂቅ የሚመስሉ እጅግ ጠቃሚ ርዕሶች ናቸው፡፡ ልትረዳው ከምትችለው በላይ ትርፋማ የሚያደርጉና አግባብ ያላቸው ነገሮች

ናቸው። በጌታ ባለኝ እድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ የበለጠ ስለነዚህ ነገሮች ስጸልይ ራሴን አገኘዋለሁ።

በክርስትና ህይወቴና በአገልግሎቴ መጀመሪያ አካባቢ ስለእነዚህ ነገሮች አልጸልይም ነበር። አሁን ግን እነዚህ መንፈሳዊ ነገሮች እጅግ እንደሚያስፈልገኝ መረዳት ጀምሬአለሁ። በእርግጠኝነት መጋቢዎች መንፈሳዊ ነገሮችን እንደሚከታተሉ ታስባላችሁ። በተቃራኒው ደግሞ ሥጋዊነታችን አጥብቀን በምንከተላቸው ነገሮች የተገለጠ ሲሆን የምንከተላቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ ደግሞ በጸሎቶቻችን የተገለጡ ናቸው።

## 5. እረኞች ስጦታዎቻቸውን ማሳደግ አለባቸው።

የጸጋ ሥጦታ ያላቸው ሰዎች በህይወታቸው የተለየ ጸጋ ያላቸው ተደርገው ሊታዩ ይችላሉ። ይህ ልክ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ከሁሉ የላቀ «የጸጋ ስጦታ›› ያላቸው ጠንክረው የሚሰሩ ሰዎች ናቸው። በስጦታቸው ዙሪያ የበለጠ ይለማመዳሉ፣ ይዘጋጃሉ እንዲሁም ያላቸውን ያፈሳሉ። ግልጽ የጸጋ ስጦታ ያለውን ሰው ቀረብ ብለዛችሁ በምትመለከቱበት ጊዜ ‹‹ ይህ ሰው የጸጋ ስጦታ ያለው ነው ወይስ በጣም ጠንክሮ የሚሰራ ነው?›› የሚል ጥያቄ ወደ አዕምሮአችሁ ይመጣል።

ፒያኖ የመጫወት፣ጎልፍ የመጫወት፣ እግር ኳስ የመጫወት ስጦታ ወ.ዘ.ተ ወዳላቸው ሰዎች ህይወት ብትሄድ ለዚህ ለመብቃት ምን ያህል ለብዙ ሰዓታት ጠንክረው ሲሰሩ ታገኛቸዋለህ። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ስጦዎቻችንን እንድናሳድግ የሚነግረን።

አንድ ጊዜ ስጦታ ከተቀበልክ ሌላ ምንም ነገር ማድረግ እንደማያስፈልግህ ታስብ ይሆናል። ጉዳዩ በተቃራኒው ነው፤ እንዲያውም ስጦታ ስላለህ ጠንክረህ መስራት ይኖርብሃል።

ለስጦታህ ማደግ ሁለንተናህን ስጥ። እግዚአብሔር በሰጠህ ስጦታ ጠንክረህ ሥራ።

> "በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፥ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል። ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ፥ ይህንም አዘውትር።"
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 4:14-15

## 6. እረኞች ታማኝነትን ማሳደግ አለባቸው።

የመጋቢነት ሥራ ሰዎችን መምራትና ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ማድረስ ነው።ሰዎች ታማኝነትን የማጉደል ዝንባሌ አላቸው። በአየር ላይ ያሉ ክፉ መናፍስት ሰዎች በእግዚአብሔርና በባሪዎቹ ላይ እንያምፁ ያነሳሳሉ። የሚያሳዝነው ነገር ብዙ አገልጋዮች ስለዚህ አስፈላጊ ነገር በቂ ግንዛቤ የላቸውም።

በዙሪያህ ሆነው የሚደግፉህ የታመኑ ሰዎች በሌሉበት ታላቅ አገልግሎት መመሥረት የማይታሰብ ነው። ስለታማኝነት ያለን መረዳት የጠለቀ መሆን ይኖርበታል። የሰዎችን ባህሪ ለመምራትና የታመኑ ተከታዮችን ለማፍራት የሚያስችሉ መርሆዎች በሚገባ ሊጠኑ ይገባል። የጠለቀ ባይሆንም እንኳ ስለነዚህ መርሆዎች ማወቅ አለብህ። ስላለመታመናቸው ሰዎችን ማስፈራራት ታማኝ አያደርጋቸውም። አለመታመን ባሳዩ ሰዎች ላይ እርግማንን ማዥጎድጎድ ተከታዮችህን ታማኝ አያደርጋቸውም።

የዲያቢሎስ ዋና ባህሪ ፍርሀት የለሽ አክብሮት ማጣት ነው። ሰይጣን ለሥልጣን አክብሮት የለውም። የአመጽ መንፈስ ስላአንተ ማንነት ወይም ስላለህ ደረጃ ግድ የለውም። ያለፍርሀት ባለሥልጣናትን ይገዳደራል፤ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ መሪዎችን የሚቃወሙ አመጽ ቀስቃሾችን ያነሳሳል።

ስለታማኝነት ማጥናትና አንተም ታማኝ መሆን አለብህ! ታማኝነትን የሚያሳድግ የአመራር ሥልት መከተል አለብህ! ስለታማኝነት እውቀት የሚያስጨብጥና ስለአለመታመን የሚያስጠነቅቅ ትምህርት ማዘጋጀት አለብህ።

> "ጢሞቴዎስ ሆይ፥ በውሸት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ፥ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ፤"
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡20

## 7. መጋቢዎች ምሳሌ የመሆን ብቃት ማሳደግ አለባቸው።

ለመንጋህ ምሳሌ መሆን የእግዚአብሔርን ቃል ከማስተማር እኩል አስፈላጊ ነው። በመሰረቱ ሰዎች የበለጠ የሚማሩት ከምታስተምራቸው ትምህርት ይልቅ ከምታሳየው ምሳሌነት ነው።

የመጋቢዎች ህይወት በማያቋርጥ ምርመራ ላይ ነው:: ትዳሩ በቤተክርስቲያን አባሉቱ ይገመገማል:: ኑሮው በሰዎች ይገመገማል:: የሚነዳው መኪና የብዙዎችን ትኩረት ይስባል:: ብዙ ሰዎች ‹‹ ምን አይነት መኪና ነው የሚነዳው? የት ነው የሚኖረው? ምንድነው የሚመገበው? ጓደኞቹ እነማናቸው? ገንዘብ የሚያገኘው ከየት ነው? የት ነው ያለው?›› የሚሉ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ::

"ቢቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ፣ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው።"

1ኛ ጢሞቴዎስ 4:12

ለዚህ አይነቱ ምርመራ ሁለት በግልጽ የማይነገሩ ምክንያቶች አሉ:: የመጀመሪያው ምክንያት በመጋቢው ላይ የሚታይ መጥፎ ምሳሌነትን ለመተቸት አጋጣሚ የሚጠብቁ ብዙዎች መኖራቸው ነው:: ሌላኛው ምክንያት ደግሞ እርሱን መከተል የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች መኖራቸው ነው::

ሰዎች ምን ያህል የመጋቢዎቻቸውን አለባበስ፣ የጸጉር አሰራር፣ የመኪና ዓይነት እና ሌሎችም ቀላል የሆኑ ነገሮችን እንደሚከተሉ ስትረዳ በጣም ትገረማለህ:: ድሆች እንደ እነርሱ ያለ ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥ ሥፍራ ይሰጠው እንደሆነ ለማወቅ የመጋቢውን ምሳሌነት ይመለከታሉ:: ባለጠጎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ተቀባይነት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ያንኑ ያደርጋሉ::

መልካም ምሳሌ የመሆንን ጥበብን አሳድግ:: የመጋቢነት ጥሪህ በሌላው ህይወትህ ላይ ገደብ እንደሚያደርግብህ መቀበል አለብህ:: ጥሩ ምሳሌ ለመሆን ከፈለግህ አንዳንድ ማድረግ የሌለብህ ነገሮች ይኖራሉ:: መልካም ምሳሌ የመሆን ጥበብ በጎችህ የሚከተሉትን መርሆ ለመቅረጽ ከምትሰጠው ትምህርት የተለየ እንደሆነ ሁልጊዜ አስታውስ::

ክርስቶስ መስቀሉን በመሸከምና ህይወቱን በማፍሰስ የተወው ምሳሌነት ከትምህርቱ ይልቅ ጎልቶ ይናገራል::

"የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍሲጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና።"

1ኛ ጴጥሮስ 2:21

ያ መስዋዕትነት የተሞላው ምሳሌነት ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ብዙዎችን አነቃቅቷል፡፡

## 8. መጋቢዎች ሁለንተናን የመስጠት አቋም ማሳደግ አለባቸው፡፡

> እስከመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ።በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፥ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል። ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አሰብ፥ ይህንም አዘውትር።
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡13-15

በአገልግሎትህ ውስጥ ሁለንተናን መስጠት ከመጠራት እኩል ዋጋ ያለው ነው፡፡ ሁለንተናን በመስጠት ካልሆነ በስተቀር ልታደርጋቸው የማትችላቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ፡፡

ሁለንተናዬን ለአገልግሎቴ በሰጠሁ ጊዜ አገልግሎቴ በአስደናቂ ሁናቴ ተለወጠ፡፡ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ሁለንተናህን መስጠት እንዳለብህ እመክርሀለሁ፡፡

አብዛኛውን ጊዜህን ከቤተክርስቲያንህ ውጭ ለአገልግሎት የምትዘዋወር ከሆነ ለመጋቢነት አገልግሎትህ ሁለንተናህን አልሰጠህም ማለት ነው፡፡ በመሰረቱ የከፊል ጊዜ መጋቢ ነህ ማለት ነው፡፡ ምዕመናንህን በየጊዜው የማትመግብ ከሆነ ለመጋቢነት አገልግሎትህ ሁለንተናህን አልሰጠህም ማለት ነው፡፡ ለጥሪህ ሁለንተናህን የምትሰጥበት ጊዜ አሁን ነው፡፡ራስህን ወደ አገልግሎትህ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወርውር፡፡ በሁለንተናህ ተንቀሳቀስ፡፡ በአገልገሎትህ ከፍተኛ መሻሻልን ታያለህ፡፡

## ምዕራፍ 35

# አንድ ወጣት ወደ እረኝነት የሚደርሰው እንዴት ነው?

"በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ፥ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው።"

1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡12

ወጣቶች የሆኑ መጋቢዎች በራስ መተማመንን ማዳበር አለባቸው። ወጣትነትህ ለአገልግሎትህ ጥሩ አጋጣሚ ሊሆንልህ ይችላል። ነገር ግን ብዙ ጊዜ እንደ ጉድለት ይታያል። የሚከተሉት ወጣትነት ተቃለው ከሚታዩባቸው ምክንያቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

## ወጣቶች ተቃልለው የሚታዩባቸው ስድስት ምክንያቶች

1. ወጣቶች ሁልጊዜ የቅድስና ጉድለት እንዳለባቸው እንዲያስቡ የሚያደርጋቸው ከፍተኛ የጾታዊ ፍላጎት መነሳሳት ይሰማቸዋል። የጾታዊ ፍላጎት ሚስጢራዊነትና ያንን የማየት ፍላጎት የብዙ ወጣቶች ግራ መጋባት ምንጭ ነው። ይህ ስሜት በእግዚአብሔር ነገር ላይ ለመካፈል ድፍረት ያሳጣቸዋል።

የማያቋርጥ ጾታዊ ፍላጎት፣ የብልት መቆም፣ ህልም፣በህልም የሚከሰት የዘር ፈሳሽመፍሰስ፣ከተቃራኒ ጾታ ጋር አብሮ መሆን፣ ለወሲብ ነክ ምስሎችና ፊልሞች፣ ለፍቅር ልብ ወለድ መጻህፍቶች ፍለጎት ማሳየት እና ሌሎችም ከወጣቶች በራስ መተማመን የሚነጥቁ ነገሮች ናቸው። ይህ ነው እንደግዲህ ወጣቶች ራሳቸውን እንዲያቃልሉና ሌሎችም እንዲያቃልሏቸው እንዲፈቅዱ የሚያደርጋቸው።

2. ውድቀትን መፍራት የወጣቶች ግራ መጋባት ምንጭ ነው። ይህ ፍርሀት የሚከሰተው በወጣቱ ዕውቀት ማጣት፣ ልምድ ማነስ፣ ከሁሉ የከፋው ደግሞ በወጣትነት ፍላጎቱ የተነሳ ነው። ፍርሀት አንድን ወጣት ከጥሪው እንዲወጣ ሊየደርገው ይችላል።

እግዚአብሔር በህይወቱ ከአስቀመጠው ዓላማ ውጭ ሊያደርው ይችላል፡፡

3. ወጣቶች ያላቸው እውቀት ውስን እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ እውቀት የምታከማቸው እድሜ በጨመርክ ቁጥር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ወጣት የሆነ ሰው ብዙ ነገር ያለማወቁን እውነታ በትክክል ይገነዘባል፡፡

4. ወጣቶች ያላቸው ልምድ ውስን እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ ህይወት እንደታሰበው እንደማይገፋ የተረዱ ጥበበኛ የሆኑ ወጣቶች የልምድ ማነስ እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡ በመሆኑም ልምድ ወዳላቸው ሰዎች የመመልከት ዝንባሌ ያሳያሉ፡፡ ሠይጣን ‹‹ይህን ከዚህ በፊት ሰርተኸው እኮ አታውቅም፣ ይህን ከዚህ ቀደም አይተኸው እኮ አታውቅም›› እያለ በጆሮአቸው ያንሾካሹካል፡፡

5. ወጣቶች ብስለት ያንሳቸዋል፡፡ ብስለት የእውቀትና የልምድ ድምር ውጤት ነው፡፡ ልምድና እውቀትን አጣምሮ ከያዘ ሰው የሚፈስ የተለየ ለዛ አለ፡፡ ውሳኔው ‹‹በእውነታ›› እና በታሪክ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ወጣት የእነዚህ ሁለት ነገሮች ጥቅም እንደጎደለበት ሁልጊዜ ይረዳል፡፡

6. ወጣቶች ልጓም በሌለው ቅንአት የተሞሉ ናቸው፡፡ የበሰሉ ሰዎች የማይነኳቸው ዓላማዎች እነርሱ አንግበው ሊነሱ ይችሉ ይሆናል፡፡ የበሰሉ ሰዎች እንደማየሳካ የደመደሙትን ነገር እነርሱ ለማሳካት ጥረት ሊያደርጉ ይችሉ ይሆናል፡፡ የበሰለው ሰው ቀድሞ በነበሩ የተሻሉ ሰዎች መፍትሄ ላልተገኘለት የቆየ ጉዳይ መፍትሄ ለመስጠት የሚታገለውን በቅንአት የተሞላ ወጣት ይመለከታል፡፡ ወጣቶች በብዙ መነሳሳት እንደተሞሉ ነገር ግን ልምድ እንደሚጎድላቸው ሁነው ይቆጠራሉ፡፡

ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ወጣቱን መጋቢ ጢሞቴዎስን ማንም ታናሽነቱን እንዳይንቀው ያሳሰበው፡፡

## ወጣቶች በአገልግሎት ውስጥ ጠቃሚ የሆኑባቸው ሰባት ምክንያቶች

ወጣቶች በተለየ ሁኔታ ለአገልግሎት ጠቃሚ ናቸው የሚባልበት ምክንያቶች አሉ።

1. **ወጣቶች የተለዩና ጠቃሚ ናቸው ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን ሲጀምር ወጣት ነበረ።** ጢሞቴዎስም ወጣት ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር በከፍተኛ ሁኔታ ተጠቅሞበታል።

2. **ወጣቶች ከፍተኛ ቅንአት ስላላቸው በአገልግሎት ውስጥ ጠቃሚ ናቸው።** ትልልቅ ሰዎች ብዙ ጊዜ በብዙ ነገር የታከቱና ተስፋ የቆረጡ ናቸው።

3. **ወጣቶች በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር ሰው ላይ የላቀ እምነት ስላላቸው በተለየ ሁኔታ ጠቃሚዎች ናቸው።** ህይወታችንና አገልግሎታችን በእምነታችን ላይ የተመሠረተ ነው። ያለ እምነት እረሱን ማስደሰት አይቻልም።

4. **ወጣቶች በውስጣቸው ያለው ጾታዊ መነሳሳት የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልገው ጥንካሬ ጠቋሚ ምልክት ስለሆነ ጠቃሚዎች ናቸው።** በመሰረቱ የጾታዊ ፍላጎት መነሳሳት መጥፋት በሌላውም የህይወት እንቅስቃሴ መነሳሳት እንደሌለ አመላካች ነው። የጾታዊ ፍላጎት መነሳሳትና ግፊት አስፈሪ ቢሆንም በመሰረቱ የመልካም ነገር ምልክት ነው።

5. **ወጣቶች በተለየ ሁኔታ ጠቃሚዎች ናቸው ምክንያቱም ብዙ የገንዘብ ችግር የለባቸውም።** በወጣትነት የዚህ ዓለም ጣጣ ብዙም አይደለም። ሰዎች በህይወታቸው ያለባቸው ኃላፊነት ሸክም ጭኖባቸው የጠጨነቁና የታከቱና ያደርጋቸዋል።

6. **ወጣቶች ልጅ የማሳደግ ኃላፊነት የሌለባቸው በመሆኑ በተለየ ሁኔታ ጠቃሚዎች ናቸው።** ልጆችን ማሳደግ ከወላጆች የሚጠበቀውን ኃላፊነት ከፍ ያደርገዋል። ወጣቶች ልጅ ከወለዱ በአገልግሎት ፍሬያማ የመሆናቸው ጉዳይ በሚያስገርም ሁኔታ እንደሚያሽቆለቁል ገብቷቸዋል።

7. **ወጣቶች በተለየ ሁኔታ ለእግዚአብሔር የሚጠቅሙ ናቸው ምክንያቱም ለህይወታቸው የተሰጣቸውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጀምሮ ለመጨረስ ጊዜ አላቸው።** እውነተኛ አገልግሎት በአብዛኛው ሁለንተናህን የሚጠይቅ ነው። ሰባ ዓመት እንኳ ብዙ ለማከናወን አይጠቅምም። አገልግሎትህን በሃምሳ አመትህ

ብትጀምር ምን ያህል ማከናወን የምትችል ይመስልሀል? ወጣቶች በጊዜ በመጀመራቸው ለእግዚአብሔር ብዙ ሊሰሩለት ይችላሉ።

## ወጣቶች በራስ መተማመን ሊያጎለብቱ የሚችሉባቸው ሰባት መንገዶች

1. ወጣቶች ብዙ በማንበብ በራስ መተማመንን ማግኘት ይችላሉ። ዕውቀት ከማንበብ ይገኛል።

"እስከመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ።"

1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡13

2. ወጣቶች የሲዲና የቪዲዮ መልዕክቶችን በማዳመጥ በራስ መተማመንን ማሳደግ ይችላሉ።

3. ወጣቶች ታሪክን በማጥናት ጥበበኞች ሊሆኑ ይችላሉ። ታሪክን በማጥናት ካለፉት ብዙ ዕውቀትን ማካበት ይችላሉ። ታሪክን የማያጠኑ ትልልቅ ሰዎችም የግል ልምዳቸው የተወሰነ ስለሆነ ዕውቀታቸው የዚያኑ ያህል ውሱን ነው።

4. ወጣቶች ስለጥበብ በመጸለይ በራስ መተማመንን ማጎልበት ይችላሉ።

5. ወጣቶች ልምድ ካላቸው ታላላቅ አባቶች ትምህርት በመቅሰም በራስ መተማመናቸውን ማጎልበት ይችላሉ።

6. ወጣቶች አስተዋይ መካሪዎችን በዙሪያቸው በማሰባሰብ በራስ መተማመንን ማጎልበት ይችላሉ።

7. ወጣቶች ከእነርሱ ቀደም ካሉ ሰዎች ስህተት በመማር በራስ መተማመንን ማጎልበት ይችላሉ። ከአንተ ቀደም ያሉ ሰዎች ስህተት የውድቀትን አቅጣጫ ያመለክትሀል። ወደፊት ምን ማስወገድ እንዳለብህ ያሳዩሀል።